# የእግዚአብሔር ልጅ በብሉይ ኪዳን

**<u>የእግዚአብሔር ልጅ በብሉይ ኪዳን</u>**

እግዚአብሔር በባሪያው በሙሴ አማካኝነት ለሕዝቡ ለእስራኤል ከሰጠው ዋነኛ ማስጠንቀቂያ አንዱ፥ ከግብፅ የወጣው የመጀመሪያው ትውልድ (The Exodus Generation) ካወቀው አምላክ ውጪ፥ ሌላ አምላክን እንዳያመልክ ነው። በዚህ ማስጠንቀቂያ መሰረት፥ እስራኤል ሊያመልክ የሚገባው ብቸኛ አምላክ ከግብፅ የወጡት አባቶቹ ያወቁትን አምላክ ብቻ ነው። አባቶቹ ያላወቁትን አምላክ የሚያመልክ ወይንም እንዲመለክ የሚጣራ ማንኛውም ሰው ፍጹም ተቀባይነት የሌለው ሲሆን፥ ቅጣቱም ሞት ነበር፦

*"6፤7፤ የእናትህ ልጅ ወንድምህ ወይም ወንድ ልጅህ ወይም ሴት ልጅህ ወይም በብብትህ ያለች ሚስትህ ወይም እንደ ነፍስህ ያለ ወዳጅህ በስውር። ና፥ ሄደን ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ ወደ አንተ የቀረቡት ከአንተም የራቁት አንተን ከብበውህ ያሉ አሕዛብ ከሚያመልኩአቸው አማልክት፥ አንተም አባቶችህም **<u>የማታውቋቸውን</u>** ሌሎች **<u>አማልክት</u>** እናምልክ ብሎ ቢያስትህ፥ **<u>እሺ አትበለው</u>**፥ 8፤ አትስማውም፤ ዓይንህም አይራራለት፥ አትማረውም፥ አትሸሽገውም፤ 9፤ ነገር ግን ፈጽመህ **<u>ግደለው</u>**፤ እርሱን **<u>ለመግደል</u>** በፊት የአንተ እጅ፥ ከዚያም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጅ በላዩ ትሁን።" (ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 13፥6-9)*

*"1፤ በመካከልህም ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሣ፥ ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ፥ 2፤ እንደ ነገረህም ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም፥ እርሱም። ሄደን **<u>የማታውቃቸውን</u>** ሌሎች **<u>አማልክት</u>** እንከተል እናምልካቸውም ቢልህ፥ 3፤ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወድዱት እንደ ሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ **<u>አትስማ</u>**።" (ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 13፥1-3)*

*"12፤13፤ አምላክህ እግዚአብሔር ልትኖርባት በሚሰጥህ በአንዲቱ ከተማህ። ክፉተኞች ሰዎች ከእናንተ ዘንድ ወጥተው። ሄደን **<u>የማታውቋቸውን</u>** ሌሎችን **<u>አማልክት</u>** እናምልክ ብለው የከተማቸውን ሰዎች አሳቱ ሲሉ ወሬ ብትሰማ፥14፤ ትፈልጋለህ፥ ትመረምራለህም፥ ትጠይቃለህም፤ እነሆም፥ እውነት ቢሆን፥ ይህም ክፉ ነገር በመካከልህ እንደ ተደረገ እርግጥ ሆኖ ቢገኝ፥ 15፤ የዚያችን ከተማ ሰዎች **<u>በሰይፍ</u>** ስለት ፈጽሞ **<u>ትመታቸዋለህ</u>**፤ ከተማይቱን፥ በእርስዋም ያለውን ሁሉ፥ እንስሳውንም በሰይፍ ስለት **<u>ታጠፋቸዋለህ</u>**።" (ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 13፥12-15)*

*"**<u>መርገምም</u>**፥ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባትሰሙ፥ ዛሬም ካዘዝኋችሁ መንገድ ፈቀቅ ብትሉ፥ ሌሎችንም **<u>የማታውቋቸውን አማልክት</u>** ብትከተሉ ነው።" (ኦሪት ዘዳግም 11:28)*

► ነገሩን በይበልጥ አስገራሚ የሚያደርገው፥ ማስጠንቀቂያው ነቢይንና ሕልም አላሚንም ማካተቱ ነው። ነቢዩ የተናገረው ቢፈጸም እንኳ፥ ነቢዩ ምልክትንና ተአምራትን ቢያሳይም እንኳ

እስራኤል ያላወቀውን እንግዳ አምላክ ከሰበከ ከላይ የተዘረዘሩት ፍርዶችና ቅጣቶች ይከተሉታል። እስራኤልም እርሱን ፈጽሞ እንዳይቀበለው ተከልክሏል። ይህ ማለት ተአምራት እንኳ የእውነተኛ አምላክነት መስፈርት አይደለም ማለት ነው። የእውነተኛ አምላክ መስፈርት "የትኛው አምላክ እስራኤልን ከግብፅ አወጣ?" ነው። እስራኤልን ከግብፅ ያላዳነ አምላክ እውነተኛው አምላክ አይደለም።

*"አምላክህ እግዚአብሔር ትሄድባት ዘንድ ካዘዘህ መንገድ ሊያወጣህ፥ **<u>ከግብፅ ምድር ካወጣችሁ ከባርነትም ቤት ካዳናችሁ ከአምላካችሁ ከእግዚአብሔር ሊያስታችሁ ተናግሮአልና</u>** ያ ነቢይ ወይም ያ ሕልም አላሚ ይገደል፤ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ አርቅ።" (ኦሪት ዘዳግም 13:5)*

*"**<u>ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ካወጣህ ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ሊያርቅህ</u>** ወድዶአልና እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ውገረው።" (ኦሪት ዘዳግም 13:10)*

አዲስ ኪዳን ደግሞ፥ እግዚአብሔር በባህርይ/መለኮት ከእርሱ ጋር አንድ የሆነ (ፊሊ 2:6 ዕብ 1:3) ከእርሱ ጋር የነበረ (ዮሐ 1:1) ሰማይና ምድርን እና በውስጣቸው ሁሉ ያለውን የፈጠረ (ቆላ 1:13-15 ዕብ 1:2 ዮሐ 1:3) እግዚአብሔር የሆነ (ዮሐ 1:1 ዕብ 1:8-12) አንዲያ (ዮሐ 3:16) **<u>ልጅ</u>** እንዳለው ያስተምራል። ይህ ልጁ የሰው ልጆችን ለማዳን (1 ዮሐ 4:9) ከሰማይ ወርዶ (ዮሐ 6:38) በስጋ እንደ መጣ (ሮሜ 8:3 1ዮሐ 3:9) ያስተምራል። ይህ ማለት በአዲስ ኪዳን አስተምህሮ መሠረት፥ አንዱ እውነተኛ አምላክ አባትና ልጅ (2 ዮሐ 1:9) ናቸው ማለት ነው። የሐዋርያትና የመላው አዲስ ኪዳን ትምህርት ይህ ነው።

✏ ኦሪትና ብሉይ ኪዳን ግን ከግብፅ የወጣው የመጀመሪያው ትውልድ ካወቀው አምላክ በቀር ሌላ አምላክ የለም ይላል። ይህ ማለት መለኮታዊውን የእግዚአብሔር ልጅ (The Divine Son of God) በብሉይ ኪዳን ማግኘት አለብን ማለት ነው። ብሉይ ኪዳን፥ እግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ እንዳለው ካላስተማረ ክርስትና ሀሰት ነው ማለት ነው። ኢዲስ ኪዳንም የእስራኤልን አምላክ በመቃረን ሌላ አምላክ ሰበከ ማለት ነው። ክርስትና እውነት ይሆን ዘንድ፥ ስለ መለኮታዊው የእግዚአብሔር ልጅ የሚያስተምረው ትምህርት የግድ ብሉይ ኪዳናዊ መሠረትና ምንጭ ሊኖረው ይገባል። አለዚያ እስራኤል ያላወቀው አምላክ ይሆናልና

♦ ብሉይ ኪዳን ግን እግዚአብሔር መለኮት የሆነ ልጅ እንዳለው ያስተምራል!

እግዚአብሔር ቢፈቅድ፥ በዚህ ጽሑፍ ብሉይ ኪዳን እንዴት እግዚአብሔር አንድ መለኮት የሆነ ልጅ እንዳለው እንደሚያስተምር እናያለን። በተጨማሪም ክርስቲያን ያልሆኑ አይሁዳውያን ተንታኞች እነዚህን አንቀጾች እንዴት እንደተረጎሟቸው እንመለከታለን።

➢ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ከብሉይ ኪዳን የምናቀርበው የመጀመሪያው ማስረጃችን እነሆ፦

**1. <u>ምሳሌ 30:3-4</u>**

*"3፤ ጥበብንም አልተማርሁም፥ **<u>ቅዱሱንም አላወቅሁትም</u>**። 4፤ ወደ ሰማይ የወጣ የወረደስ ማን ነው? ነፋስንስ በእጁ የጨበጠ ማን ነው? ውኃንስ በልብሱ የቋጠረ ማን ነው? የምድርን ዳርቻ ሁሉ ያጸና ማን ነው? ይህን ታውቅ እንደ ሆንህ፥ **<u>ስሙ</u>** ማን **<u>የልጁስ ስም</u>** ማን ነው?" (መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 30፥3-4)*

በዚህ ስፍራ የያቄ ልጅ አጉር፤ ጥበብን እንዳልተማረና፥ ከሰውም ሁሉ ይልቅ ማስተዋል እንደሌለው ሲናገር እንመለከታለን። ከዚያም ቅዱሱን እንደማያውቅ ከተናገረ በኋላ በቁ.4 ላይ የእግዚአብሔርና የልጁ ስም ማን እንደሆነ የሚያውቅ ካለ ይጠይቃል

► አንኳር ሀሳቦቹን ነጥብ በነጥብ እንመልከት

1. "ቅዱሱ" የሚለው ቃል ብዙ ቀጥር ነው

በቁ.3 ላይ አጉር ቅዱሱን አላውቅም ሲል፥ ቃሉን የተጠቀመው በብዜት ነው። ቃሉ "ቃዶሺም/קדשים" ሲሆን በቀጥታ ሲተረጎም "ቅዱሳን" ማለት ነው። በዕብራይስጥ በ"_ **<u>ים/ኢም</u>** " ካለቀ ቃሉ ብዜት ነው ማለት ነው።

*"ጥበብንም አልተማርሁም፥ **<u>ቅዱሱንም</u>** አላወቅሁትም።" (መጽሐፈ ምሳሌ 30:3-4)*

*ולא־למדתי חכמה ודעת **<u>קדשים</u>** אדע(Proverbs 30:3)*

✒ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና፥ ይህ ቃል በሌሎች ስፍራዎችም ላይ ጥቅም ላይ እንደዋለና፤ ሁሌም የሚገባው ከአንድ በላይ አካላትን ለማመልከት እንደሆነ እንረዳለን። ይህ የጸሐፊውን እሳቤ በይበልጥ ግልፅ አድርጎ ያሳየናል። ለምሳሌ፦

*"እሁንም ጥራ የሚመልስልህ አለን? **<u>ከቅዱሳንስ</u>** (**<u>קדשים</u>**) ወደማናቸው ትዞራለህ?" (ኢዮብ 5፥1)*

*"ፈቃድህ ሁሉ በምድር ባሉት **<u>ቅዱሳንና</u>** (**<u>קדשים</u>**) ክቡራን ላይ ነው።" (መዝሙረ ዳዊት 16:3)*

*"የተራሮችም ሸለቆ እስከ አጸል ይደርሳልና በተራሮች ሸለቆ ትሸሻላችሁ፤ በይሁዳም ንጉሥ በዖዝያን ዘመን ከሆነው ከምድር መናወጥ ፊት እንደ ሸሻችሁ ትሸሻላችሁ፤ አምላኬ እግዚአብሔርም **<u>ከቅዱሳኑ</u>** (**<u>קדשים</u>**) ሁሉ ጋር ይመጣል።" (ትንቢተ ዘካርያስ 14:5)*

*"5፤ አቤቱ፥ ሰማያት ተኣምራትህን እውነትህንም ደግሞ **<u>በቅዱሳን</u>** **<u>(((קדשים</u>** ማኅበር ያመሰግናሉ። 6፤ እግዚአብሔርን በሰማይ የሚተካከለው ማን ነው? ከአማልክትስ ልጆች እግዚአብሔርን ማን ይመስለዋል? 7፤ **<u>በቅዱሳን</u>** **<u>(((קדשים</u>** ምክር እግዚአብሔር ክቡር ነው፤ በዙሪያው ባሉት ሁሉ ላይ ታላቅና ግሩም ነው።" (መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 89:5-7)*

► ይህንንም ሀቅ የተረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚያን፥ ከዕብራይስጡ ጋር በሚስማማ መልኩ በትክክል **ቅዱሳን** **(Holy Ones)** በማለት ተርጉመውታል፦

*"Nor have I learned wisdom, Yet the knowledge of **Holy Ones** I know."*

*(Proverbs 30:3) (YLT)*

*"I have not learned wisdom, nor have I knowledge of the **holy ones.**"*

*(Prov 30:3) (NRSV)*

*"Neither have I learned wisdom, nor, the knowledge of the **Holy Ones**, can I acquire."*

*(Prov 30:3) (EBR)*

► እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን "ቅዱሳን" ተብሎ ከተጠራባቸው ክፍሎቸ አንዱ ይህ ነው (ኢያ 24:19 ምሳ 9:10 ኢዮ 30:3) እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ በብዙ ግሶች ተጠርቷል

[ http://www.ewnetlehulu.org/am/divine-plurality/ ]

✏ ሌላው ሊስተዋል የሚገባው ነገር፥ በምሳሌ 30 አውድ፥ ቅዱሳን ተብለው የተጠሩት እግዚአብሔር እና ልጁ መሆናቸው ነው። በቁ.3 ላይ ቅዱሳኑን እንደማያውቅ ከተናገረ በኋላ ቅዱሳን ያለው እግዚአብሔርንና ልጁን መሆኑን ግልጽ ያደርጋል። በቁ.3 ላይ ቅዱሳኑን እንደማያውቅ ከተናገረ በኋላ፥ በቁ.4 ላይ "..ይህን ታውቅ እንደ ሆነ ስሙ ማነው የልጁስ ስም ማነው?" ብሎ የእግዚአብሔርንም የልጁንም ስም የሚያውቅ ካለ ይጠይቃል። ይህ ማለት የእግዚአብሔርንም የልጁንም ስም አያውቅም ማለት ነው። ስማቸውን እየጠየቀ ነው። ይህ በቁ.3 ላይ አላወኳቸውም ያላቸው ቅዱሳን ማን እንደሆኑ ያሳያል። እግዚአብሔርና ልጁ ናቸው። ይህ በግልጽ መለኮት በብዙ ግስ ሲጠራ አብን እና ልጁን ለማመልከት እንደሆነ ያሳያል። አጉር የእግዚአብሔርንና የልጁን ስም የጠየቀው፥ መለኮትን ቅዱሳን በማለት በጠራበት አውድ ነውና።

2. የእግዚአብሔርን ስም ይጠይቃል

አጉር በቁ.4 ላይ የእግዚአብሔርን የተለያዩ ባህሪያት ከዘረዘረ (ንፋስን በእጁ የጨበጠ፥ ውኃን በልብሱ የቋጠረ ወዘተ) በኋላ ስሙን ይጠይቃል። ለምንድነው ስሙን የጠየቀው?

► በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ስም ባህርይውን ያመለክታል። ስለ እግዚአብሔር ባህርይ/ህላዌ ወይንም ማንነት መናገር ሲያስፈልግ "**ስሙ**" ይባላል።

የእግዚአብሔርን ስም ማስቆጣት (መዝ 74:18) እግዚአብሔርን ማስቆጣት ነው፥ የእግዚአብሔርን ስም መውደድ (መዝ 69:36) እግዚአብሔርን መውደድ ነው፥ ለእግዚአብሔር ስም መዘመር (መዝ 7:17) ለእግዚአብሔር መዘመር ነው፥ የእግዚአብሔርን ስም ማወቅ (መዝ 9:10) እግዚአብሔርን ማወቅ ነው

የእግዚአብሔር ስም ራሱ እግዚአብሔርን የሚያመለክት በመሆኑ፥ በ2 ሳሙ 6:2 ሁለት ግዜ ተደግሞ እንመለከተዋለን፦

*"ዳዊትና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሕዝብ ሁሉ በይሁዳ ካለች ከበኣል ተነሥተው በኪሩቤል ላይ በተቀመጠ በሠራዊት ጌታ **በእግዚአብሔር ስም** የተጠራውን የእግዚአብሔርን ታቦት ከዚያ ያመጡ ዘንድ ሄዱ።" (መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 6:2)*

*ויקם וילך דוד וכל־העם אשר אתו מבעלי יהודה להעלות משם את ארון האלהים אשר נקרא **שם שם יהוה** צבאות ישב הכרבים עליו (2 Samuel 6:2)*

በአማርኛው ትርጉም ላይ በቀጥታ ባይተረጎምም፥ በዕብራይስጡ ግን የሚለው "..በእግዚአብሔር ስም ስም የተጠራው" ነው። ስም ሁለቴ የተደገመበት ምክንያት፥ የእግዚአብሔር ስም ራሱ እግዚአብሔርን ለማመልከት ጥቅም ላይ ስለሚውል ነው። የእግዚአብሔር ስም ሲባል ራሱ እግዚአብሔር ማለት ነው። ስለዚህ በ2 ሳሙ 6:2 **"ስም"** የሚለው የመጀመሪያው ቃል የእግዚአብሔር ማንነት የሚያመለክት ነው። ሁለተኛው አገባብ ደግሞ እንደ መጠሪያ እያገለገለ ነው። ስለዚህ 2 ሳሙ 6:2 "የእግዚአብሔር ስም ስም" ሲል "የእግዚአብሔር ስም" ማለቱ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ስም ማንነቱን ወይንም ባህርይውን እንደሚያመለክት በግልጽ ያሳያል። ሌላ ምሳሌ፦

*"እነሆ፥ **የእግዚአብሔር ስም** ከሚነድድ ቍጣ ከሚትጐለጐልም ጢስ ጋር ከሩቅ **ይመጣል**፤ **ከንፈሮቹም** ቍጣን የሞሉ ናቸው፥ ምላሱም እንደምትበላ እሳት ናት፤" (ትንቢተ ኢሳይያስ 30:27)*

በዚህ ስፍራ ነቢዩ ኢሳያስ የእግዚአብሔር ስም ከሚነድ ቁጣ፥ ከሚትጎለጎል ቁጣ ጋር እንደሚመጣ ይናገራል። ጨምሮም በከንፈሮቹ ቁጣ እንደተሞሉ ይናገራል። ይህ ለአንድ እውነተኛ ማንነት የሚሰጥ አገላለጽ ነው። መጠሪያ ከሩቁ ሊመጣ አይችልም፥ ቁጣንም ሊሞላ አይችልም። ስለዚህ በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር ስም ሲል ስለ ማንነቱ እየተናገረ ነው ማለት ነው። የእግዚአብሔር ስም ይመጣል ማለት ራሱ እግዚአብሔር ይመጣል ማለት ነው። ራሱ እግዚአብሔር በቁጣ ተሞልቶ ይመጣል ማለት ነው። ስም የእግዚአብሔርን ማንነት እያመለከተ ነውና። ይህ ስም የእግዚአብሔርን ባህርይ ወይንም ማንነት እንደሚያመለክት የሚያሳይ ሌላ ማስረጃ ነው።

✏ ስለዚህ አጉር ስሙ ማነው ሲል፥ እርሱ ማነው? ከመታወቅ ያለፈ ነው ማለቱ ነው።

የእግዚአብሔር ባህርይ ከመታወቅና ከመመርመር በላይ መሆኑን እየተናገረ ነው። ለዚያም በቁ.3 ላይ አላወኩትም ያለው። ከመታወቅ በላይ ነውና

አጉር ስሙ ማነው ሲል "ያሕዌ" የሚባለው የእግዚአብሔር ስም ማነው እያለ አይደለም። ምክንያቱም ሁሉም እስራኤላዊ "ያሕዌ" የተባለውን ስም ያውቀዋልና። በሲና ተራራ ተገልጦ ራሱን የጠራው በዚያ ስም ነው (ዘጽ 20:2) ያም ስሙ የዘላለም ስሙ ነው (ዘጽ 3:16) የእስራኤል ሕዝብም ከግብፃውያን ከዳነ በኋላ እግዚአብሔርን የጠራበት ስሙ ያ ነው (ዘጽ 15:3) ስለዚህ "ያሕዌ" የሚለውን ስም ላያውቅ የሚችልበት ሁኔታ የለም።

ሲቀጥል፥ አጉር በራሱ "ያሕዌ" የሚለውን ስም ያውቀዋል፦

*"እንዳልጠግብ እንዳልክድህም። **<u>እግዚአብሔርስ (הוהי)</u>** ማን ነው? እንዳልል፤ ድሀም እንዳልሆን እንስልሰርቅም፥ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል።" (መጽሐፈ ምሳሌ 30:9)*

አጉር የእግዚአብሔርን ስም እያወቀ ለምን የእግዚአብሔርን ስም ጠየቀ ብለን ብንጠይቅ፤ መልሱ እየተናገረ የነበረው ከመታወቅ በላይ ስለሆነው ባህሪው እንጂ ስለ መጠሪያ ስሙ አይደለም የሚል ይሆናል።

♦ነገር ግን ስሙ ማነው ያለው ለእግዚአብሔር ብቻ አይደለም፥ ለልጁም ነው! የልጁንም ስም አያውቀውም

ይህ ማለት፥ በምሳሌ 30 መሰረት እግዚአብሔር፤ ልክ እንደ እርሱ ከመታወቅ በላይ የሆነ ልጅ አለው ማለት ነው። ልክ እንደርሱ የማይመረመር ባህርይ ያለው ልጅ አለው ማለት ነው። ወይንም መለኮት የሆነ ልጅ አለው ማለት ነው። ይህ እግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ እንዳለው ከምንም በላይ የሚያሳይ ማስረጃ ነው።

ታዲያ ይህ መለኮታዊው የእግዚአብሔር ልጅ ማነው?

ከላይ ለመነጋገር እንደሞከርነው፥ እውነተኛው አምላክ እስራኤልን ከግብፅ በማውጣት ከባርነት ያዳናቸው አምላክ ነው። ከዚህ አምላክ ውጪ ሌላ አምላክ የሌለ ሲሆን፥ የመጀመሪያው የዘጽአት ትውልድም ያወቀው አምላክ ይህ ነው። ለዚህም ነው "..አባቶቻችሁ ያላወቋቸውን" ብሎ በሀይል የሚያስጠነቅቃቸው። ከግብፅ የወጡት የእስራኤላውያን አባቶች ያወቁት አምላክ ብቻ ትክክለኛው አምላክ ነው።

ስለዚህ፥ ይህ አጉር የሚዘምርለት የእግዚአብሔር ልጅ በእርግጥም መለኮት ከሆነ የግድ በዚያ ትውልድ መታወቅ አለበት። የግድ እስራኤልን ከግብፅ አውጥቶ ማዳን አለበት። የግድ የእስራኤል አምላክ መሆኑ መገለጽ አለበት። ከላይ በብዙ ማስረጃዎች እንዳየነው ደግሞ፥ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ መለኮት ነው። ልክ እንደ አባቱ እንደ እግዚአብሔር የማይመረመርና ከቶውኑ

ሊታወቅ የማይችል ስም/ባህርይ አለው። ስለዚህ ፍጡር ሊሆን አይችልም። ይህ ማለት፥ የዚህ የእግዚአብሔር ልጅ እውነተኛ ማንነት የሚታወቀው በዘጽአቱ ታሪክ ነው ማለት ነው። ታዲያ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ማነው?

በምሳሌ 30 አጉር የዘመረለት የእግዚአብሔር ልጅ፥ የእግዚአብሔር መልአክ ነው!

በምሳሌ 30 ላይ አጉር የዘመረለት የእግዚአብሔር ልጅ መልአኩ ነው። እርሱን ነው የማይመረመር ባህርይ እንዳለው በመናገር አጉር ያመለከው። ከዚህ በፊት እንደተነጋገርነው፥ መልአክ የሚለው ቃል " **/מלאךማልአኽ"** ሲሆን መልእክተኛ ማለት ነው። አሰራርን እንጂ ባህርይን የሚያመለክት ቃል አይደለም። የተላከ ማንኛውም አካል መልአክ ተብሎ ይጠራል። ቃሉ ለፍጡራን መናፍስት፥ ለሰዎች፥ ለመለኮትም ጥቅም ላይ ውሏል። የመልአኩ/መልእክተኛው ባህርይ የሚለየው በዙሪያው ባለው አውድ ነው። ለምሳሌ፦

*"**ካህኑ** የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር **መልእክተኛ** ነውና ከንፈሮቹ እውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፥ ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል።" (ትንቢተ ሚልክያስ 2:7)*

*"כי־שפתי **כהן** ישמרו־דעת ותורה יבקשו מפיהו כי **מלאך** יהוה־צבאות הוא" (Malachi 2:7)*

በዚህ ስፍራ ካህኑ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደሆና የእውነት ሕግን ማስተማር እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንመለከታለን። "መልእክተኛ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል "**מלאך**" ሲሆን በቀጥታ ሲተረጎም መልአክ ማለት ነው። ሚል 2:7 "..ካህኑ የእግዚአብሔር መልአክ ስለሆነ.." ነው የሚለው። ነገር ግን ካህኑ ሰው ነው፥ መልአክ ተብሎ ስለተጠራ ለማገልገል ከተፈጠሩ መናፍስት አንዱ ነው ማለት አይደለም። ስለተላከ፥ በአሰራሩ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ስለሆነ መልአክ ተብሎ ተጠራ እንጂ። በዙሪያው ያለው አውድ ግልፅ እንደሚያደርገው፥ መልአክ የተባለው ካህን ሰው ነው። ለዚያ ነው የመልአኩ/መልእክተኛው ባህርይ በዙሪያው ባለው አውድ የሚታወቅ ነው ያልነው። ሌላ ምሳሌ፦

*"የእግዚአብሔርም **መልእክተኛ** ሐጌ በእግዚአብሔር መልእክት ሕዝቡን። እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፥ ይላል እግዚአብሔር ብሎ ተናገረ።" (ትንቢተ ሐጌ 1:13)*

*"ויאמר חגי **מלאך** יהוה במלאכות יהוה לעם לאמר אני אתכם נאם־יהוה" (Haggi 1:13)*

በዚህ ስፍራም፥ ነቢዩ ሐጌ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ተብሎ ሲጠራ እንመለከታለን። አሁንም "መልእክተኛ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል "**מלאך**" ሲሆን በቀጥታ ሲተረጎም መልአክ ማለት ነው። ሐጌ 1:13 በቀጥታ ሲተረጎም "..የእግዚአብሔር መልአክ ሐጌ.." ነው

የሚለው። ነገር ግን ነቢዩ ሐጌ ሰው እንጂ አገልጋይ መንፈስ አይደለም። መልአክ ተብሎ የተጠራው በአሰራሩ እንጂ በባህርይው ሰው ነው። ስለተላከ፥ የመልእክተኝነት ግብር ስለነበረው መልአክ ተብሎ ተጠራ እንጂ በባህርይው ሰው ነው። ሰው መሆኑ በዙሪያው ባለው አውድ የሚታወቅ ነው ያልነው ለዚህ ነው። ስለዚህ መልአክ መልእክተኝነትን እንጂ ባህርይን አያመለክትም

♦ ይህ የእግዚአብሔር መልአክ በቁጥቋጦው ለሙሴ የተገለጠ ነው (ዘጽ 3:2) እስራኤልን ከግብፅ ያወጣ ነው (መሳ 2:1) በእስራኤል ፊት ሲሄድ የነበረ ነው (ዘጽ 14:19 ዘጽ 23:23) እስራኤልን በምድረ በዳ የጠበቀ ነው (ዘጽ 23:20) እስራኤልን ወደ ቃል ኪዳኑ ምድር ያገባ ነው (ዘጽ 23:23) የእስራኤልንም ያዳነ ነው (ኢሳ 63:9) በቀጥታ እግዚአብሔር ነኝ ብሏል (ዘፍ 31:10-13) በተጨማሪም እግዚአብሔር በሲና ተራራ ተገልጦ፥ ስሙ በውስጡ እንደሆነና ሀጢአታቸውን ይቅር እንደማይል ለመጀመሪያው የዘጽአት ትውልድ ተናግሯል (ዘጽ 23:21) እርሱንም እንዲሰሙት አዟቸዋል (ዘጽ 23:22)። ከላይ የተዘረዘሩት ነገሮች በሙሉ ራሱ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረጋቸው ነገሮች እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል

[ ዘጽ 20:2 ዘዳ 1:30 ዘዳ 32:10 ዘዳ 8:9 ዘጽ 13:5 ዘዳ 33:29 ]

ይህ መልአኩ ልክ እንደ እግዚአብሔር መለኮታዊ ስልጣን ያለው መሆኑንና እስራኤልን ከግብፅ ያወጣው አምላክ መሆኑን ያሳያል። በዚህም ምክንያት በተደጋጋሚ እግዚአብሔር ተብሏል (ዘጽ 3:6 ዘጽ 19:11 ዘጽ 19:20-21 ዘጽ 24:1 ዘጽ 24:11) የእስራኤል አምላክ ተብሏል (ዘጽ 24:10) ስለዚህ መልአኩ እስራኤል ከመጀመሪያው ጀምሮ ያወቀው፥ ከግብፅ ምድር ያወጣው አምላኩ ነው ማለት ነው። አጉር በምሳሌ 30:3-4 የእግዚአብሔር ልጅ በማለት የሚጠራው እርሱን ነው።

♦ በዚያ ቦታ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው መልአኩ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

መልአኩ አጉር የዘመረለት ልጅ መሆኑን የምናውቅበት ብዙ መንገዶች አሉ። ማስረጃዎቹ እነሆ፦

*"በፊቱ ተጠንቀቁ፥ ቃሉንም አድምጡ፤ **ስሜም** በእርሱ ስለ ሆነ **ኃጢአት** ብትሠሩ **ይቅር አይልምና** አታስመርሩት።" (ኦሪት ዘጸአት 23:21)*

► በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ተገልጦ ለእስራኤል ሕዝብ ስለ መልአኩ ሲናገር እንመለከታለን። በፊቱ እንዲጠነቀቁና፥ ቃሉን እንዲያዳምጡ ከነገራቸው በኋላ ስሙ በውስጡ ስለሆነ ሀጢአታቸውን ይቅር እንደማይላቸው ይነግራቸዋል

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው፥ ሀጢአትን ይቅር የማይለው እግዚአብሔር ነው። ይህ ማለት ሀጢአትን በተመለከተ ለመማርም፥ ለመኮነንም ስልጣን ያለው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ይህ እግዚአብሔር ብቻ የሚያደርገው ነገር ሲሆን ከእግዚአብሔር ልዩ ባህርያት መካከል

አንዱ ነው። (ዘጽ 20:7 ዘጽ 34:7 ዘኁ 14:18 ዘዳ 5:11 ኢያ 24:19)

መልአኩ ግን ይህ የመለኮት ብቸኛ ባህርይ ሊኖረው ቻለ። ምክኒያቱ ምንድነው ስንል፥ የእግዚአብሔር ስም በውስጡ በመሆኑ እንደሆነ እንረዳለን። ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው፥ ስም ባህርይን ወይም ማንነትን ያመለክታል። ስለዚህ መልአኩ ሀጢአታቸውን ይቅር የማይለው የእግዚአብሔር ስም በውስጡ ስለሆነ ነው። መልአኩ ልክ እንደ እግዚአብሔር ሀጢአትን በተመለከተ ስልጣን ሊኖረው የቻለው ከእግዚአብሔር ጋር የባህርይ አንድነት ስላለው ነው። ሀጢአትን በተመለከተ ስልጣን ያለው መለኮት ብቻ ነውና

በምሳ 30:4 ላይም ከዚህ ጋር አንድ አይነት የሆነ ነገርን እናገኛለን። በዚያ ስፍራ እግዚአብሔርና ልጁ አንድ ስም እንዳላቸው አጉር ይናገራል። የሁለቱም ስም (ባህርይ) ከመታወቅ በላይ ነው። ልጁ ልክ እንደ እግዚአብሔር ከመመርመር በላይ የሆነ ስም (ባህርይ) ሊኖረው የቻለው፥ ከእርሱ ጋር የባህርይ አንድነት ስላለው ነው። ከመመርመር በላይ መሆን የመለኮት ብቸኛ ባህርይ ነውና። ይህ በግልጽ አጉር የዘመረለት ልጅ፥ የእግዚአብሔር ስም (ባህርይ) በውስጡ ያለው መልአክ መሆኑን ያረጋግጣል። እግዚአብሔር በባህርይው የሆነውን ነገር ሁሉ የሆነው እርሱ ነውና

➢ ሲቀጥል፥ ያ መልአክ/መልእክተኛ በባህርይው የማይመረመር መሆኑን መናገሩ አጉር የዘመረለት ልጅ እርሱ መሆኑን ያሳያል

*"የእግዚአብሔርም **መልአክ**። **ስሜ ድንቅ ነውና** ለምን ትጠይቃለህ? አለው።" (መጽሐፈ መሳፍንት 13:18)*

► በዚህ ስፍራ የእግዚአብሔር መልአክ ለሳምሶን ወላጆች ለማኑሄና ለባለቤቱ ተገልጦ የሰራውን ስራ እናነባለን። ልጅ እንደሚወልዱና ያም ልጅ ለእግዚአብሔር የተለየ እንደሚሆን ይነግራቸዋል። ይህንን ሲላቸው እርሱ የነገራቸው ቃል ሲፈጸም ያከብሩት ዘንድ ስሙን ይጠይቀዋል

መልአኩ ግን ስሜ ድንቅ ስለሆነ ለምን ትጠይቀኛለህ ይለዋል። ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ስም ማንነትን ወይንም ባህርይን ያመለክታል። ስለዚህ መልአኩ ስሜ ድንቅ ነው ሲል፥ ባህርዬ ድንቅ ነው፥ ከመታወቅ በላይ፥ ከአዕምሮ በላይ ነኝ ማለቱ ነው

በመሳ 13:18 ላይ "**ድንቅ**" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል "**פלאי/ፓላይ**" ሲሆን ከመታወቅ በላይ መሆንን ያመለክታል። ይህ ቃል በዚህ ሥፍራ ላይ ባለው አገባብ፥ ሁለቴ ብቻ ሲሆን የተጠቀሰው የመጀመሪያው፥ በዚሁ በመሳ 13:18 ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በመዝ 139:6 ነው፦

*"እውቀትህ ከእኔ ይልቅ **ተደነቀ**ች፤ በረታች፥ ወደ እርስዋም **ለመድረስ አል ችልም**።" (መዝሙረ*

*ዳዊት 139:6)*

በዚህ ስፍራ፥ ዳዊት ለእግዚአብሔር "እውቀትህ ከእኔ ይልቅ ተደነቀች፥ በረታች፥ ወደ እርሷም መድረስ አልችልም" ይላል። ይህ ማለት የእግዚአብሔር እውቀት ከዳዊት እውቀትና መረዳት እጅጉን የላቀ ነው ማለት ነው። በምንም መልኩ ሊያውቀው ወይንም ሊመረምረው እንደማይችል እየተናገረ ነው። "ተደነቀች" ሲል የእግዚአብሔር እውቀት ከመታወቅና ከመመርመር በላይ መሆኑን የሚገልጽ ነው። ለዚያም ነው ተደነቀች ብሎ ልደርስባት አልችልም ያለው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር እውቀት ድንቅ ነውና፥ ማንም ሊደርስበት አይችልም። ይህ "ድንቅ" የሚለው ቃል ከመመርመር፥ ከመታወቅ በላይ መሆንን እንደሚያመለክት ግልጽ ማስረጃ ነው። ስለዚህ መልአኩ ስሜ ድንቅ ነውና ለምን ትጠይቃለህ ሲለው፥ እኔ ከመታወቅ በላይ ነኝና ለምን ማን እንደሆንኩ ትጠይቃለህ ማለት ነው። ስም ባህርይን ሲያመለክት ድንቅ መባሉ ደግሞ ከመታወቅ በላይ መሆን ያመለክታልና

ከዚያም በቁ.22 ላይ፥ ማኑሄ የተገለጠለት መልአኩ መሆኑን ካወቀ በኋላ "እግዚአብሔር" በማለት ይጠራዋል። ይህ ማኑሄ ስለ እግዚአብሔር መልአክ የቀደመ እውቀት እንደነበረውና፤ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያምን እንደነበር በግልጽ ያሳያል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በማለት የጠራው መልአኩ መሆኑን ካወቀ በኋላ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር በማለት ከጠራው በኋላ፥ እርሱን በማየታቸው እንደሚሞቱ ለሚስቱ ይነግራታል

ለምን የእግዚአብሔርን መልአክ ማየታቸው ሞትን የሚያስከትል መሰለው? ማኑሄ ሞትን ሊፈራ የቻለበት ምክንያት፥ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ፥ ሕዝቡ ወደ ተራራው ወጥተው ካዩት እንደሚሞቱ የተናገረለት እግዚአብሔር መልአኩ በመሆኑ ነው (ዘጽ 19:21) ስሜ (መለኮት) በውስጡ ነው ያለለት እርሱ ስለሆነ ነው (ዘጽ 23:21) እነ ሙሴም ስላዩት እጁን ያላነሳባቸው እግዚአብሔር እርሱ ነው (ዘጽ 24:11) ማኑሄም ይህንን ሁሉ ስለሚያውቅ፤ የተገለጠላቸው መልአክ እርሱ መሆኑን ሲረዳ፥ እርሱን በማየታቸው እንደሚሞቱ ተናገረ

➢ ይህ በግልጽ መልአኩ፥ አጉር የዘመረለት ልጅ መሆኑን ያሳያል። አጉር የዘመረለት ልጅ፥ በባህርይው ከመታወቅ በላይ ነው። ለማኑሄ የተገለጠውም መልአክ ባህርይው ከመታወቅ በላይ መሆኑን መስክሯል። ይህ ልጁ መልአኩ መሆኑን በግልጽ ያሳያል

*"ያዕቆብም። ስምህን ንገረኝ ብሎ ጠየቀው። እርሱም። **ስሜን** ለምን ትጠይቃለህ? አለው። በዚያም ስፍራ ባረከው።" (ኦሪት ዘፍጥረት 32:29)*

► በዚህ ስፍራም እንዲሁ የእግዚአብሔር መልአክ በባህርይው ከመታወቅ በላይ መሆኑን ሲናገር እንመለከታለን። ያዕቆብን ሊለየው ሲል፥ ስሙን ሲጠይቀው ለምን ስሜን ትጠይቀኛለህ ይለዋል። ይህ ማለት ስሙ/ማንነቱ ከአዕምሮ በላይ ነው ማለት ነው። ይህ ማለት መልአኩ አጉር የዘመረለት ልጅ ነው ማለት ነው።

በዚህም ምክንያት ያዕቆብ "እግዚአብሔርን" በማለት ይጠራዋል (ቁ.30) እርሱን አይቶ በሕይወት በመትረፉም ይደነቃል። ከዚያም ያንን ቦታ "ጵኒኤል/የእግዚአብሔር ፊት" በማለት በመለኮታዊ ስያሜ ይሰይመዋል። መለኮታዊ ስም (theophoric name) የእግዚአብሔርን ስም የያዘ ስም ሲሆን ግህዶተ መለኮት (የአምላክ መገለጥ) ሲኖር የሚሰየም ስም ነው። ይህ ተግባር የአምልኮ ተግባር ሲሆን፥ የሚሰየመው ስያሜ መለኮት በዚያ ስፍራ ተገልጦ ከሰራው ስራ ጋር የሚሄድ ስም ነው። ያዕቆብም መለኮትን ፊት ለፊት ስላየ ቦታውን "የእግዚአብሔር ፊት" በማለት ሰየመው። (ዘፍ 16:14 ዘፍ 22:14 ዘፍ 28:19)

ይህም ሀቅ በሆሴ 12:3-6 ተረጋግጦ እናገኘዋለን። በዚያ ስፍራ ከያዕቆብ ጋር የታገለው መልአክ፥ "እግዚአብሔር/ያሕዌ" "አምላክ/ኤሎሂም" እና "የሠራዊቱ አምላክ" ተብሎ ተጠርቷል። አምላክነት ደግሞ አይመረመርነት ስለሆነ (ኢዮ 36:26) በባህርይው ከመታወቅ በላይ የሆነው ልጁ፥ መልአኩ ነው ማለት ነው።

*"የእግዚአብሔርም **ሠራዊት** አለቃ ኢያሱን። አንተ የቆምህበት ስፍራ **የተቀደሰ** ነውና **ጫማህን ከእግርህ አውልቅ** አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።" (መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 5:15)*

► በዚህ ስፍራ፤ የእግዚአብሔር መልአክ ኢያሱን አምልኮ ሲጠይቀው እንመለከታለን። የቆመበት መሬት ቅዱስ በመሆኑ ጫማውን እንዲያወልቅ ያዘዋል። መልአኩ ከመገለጡ በፊት ያ ስፍራ ቅዱስ አልነበረም። ነገር ግን እርሱ በመገለጡ ምክንያት፥ ያ ስፍራ ቅዱስ ሆነ

መልአኩ ኢያሱን የጠየቀው አምልኮ እግዚአብሔር ሙሴን የጠየቀው አምልኮ ነው (ዘጸ 3:4-5) በተጨማሪም በቀጣዩ ምዕራፍ "እግዚአብሔር" ተብሏል (ኢያ 6:2) በሌላም ቦታ እንዲሁ ይህ የሰራዊት አለቃ፥ የሰራዊት አምላክ ተብሎ ተጠርቷል (ሆሴ 12:5-6) ቅዱሱ ነውና እርሱ ስለተገለጠ፥ ያ ስፍራ ተቀደሰ

*"2፤ የእግዚአብሔርም **መልአክ** በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል **ታየው**፤ እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ። 3፤ ሙሴም። ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ። 4፤ እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ **እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ**። ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ አለ። 5፤ እርሱም። እነሆኝ አለ። ወደዚህ አትቅረብ፤ አንተ የቆምህባት ስፍራ **የተቀደሰች** መሬት ናትና **ጫማህን ከእግርህ አውጣ** አለው።"*

*(ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 3:2-5)*

በምሳሌ 30:3 ላይ አጉር እግዚአብሔርና ልጁን ቅዱሳን በማለት ይጠራል። ይህ በግልጽ እንደሚያሳየው ከመታወቅ በላይ የሆነው ልጅ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ማለት ነው። መልአኩም አጉር የዘመረለት ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ፤ ለኢያሱ በተገለጠ ግዜ

ስፍራው ስለተቀደሰ ጫማውን እንዲያወልቅ በማዘዝ አምልኮን ጠየቀው። በዚያውም አውድ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠራ፥ ከተማይቱን እንደሚሰጠውም ቃል ገባለት። ይህ ለኢያሱ የተገለጠው መልአክ፤ አጉር የዘመረለት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በግልጽ ያሳያል (ኢያ 6:2-5)

➢ አይመረመርነት የመለኮት ብቸኛ ባህርይ ሆኖ ሳለ እንዴት መልአኩ ልክ እንደ እግዚአብሔር ከመታወቅ በላይ ሊሆን ቻለ?

አዎ፤ ከመታወቅ በላይ መሆን የመለኮት ባህርይ ብቻ ነው። የትኛውም ፍጡር ከመታወቅ በላይ አይደለም

*"እነሆ፥ **<u>እግዚአብሔር</u>** ታላቅ ነው፥ እኛም **<u>አናውቀውም</u>**።" (መጽሐፈ ኢዮብ 36:26)*

*"ወይስ ሁሉን የሚችል **<u>አምላክ</u>** ፈጽመህ **<u>ልትመረምር</u>** ትችላለህን?" (መጽሐፈ ኢዮብ 11:7)*

መልአኩ ግን ከመታወቅ በላይ ሊሆን የቻለበት ምክንያት የእግዚአብሔር ስም (መለኮት) በውስጡ ስላለ ነው (ዘጽ 23:21) ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ባሕርይ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ልክ እንደ እግዚአብሔር ከመታወቅ ያለፈ ነው

## <u>የአይሁድ ተንታኞች ምሳሌ 30:3-4 በተመለከተ ምን አሉ?</u>

ይህን ቃል ያብራሩት አይሁድ እጅግ አስገራሚ ምስክርነት ሰጥተዋል። በዚህ ቦታ ላይ "**ልጅ**" የተባለው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን መስክረዋል።

“Who has ascended to heaven and come down’, is the Holy One, blessed be His name – for God rose up with a shout and came down on Mt. Sinai… And he answers, ‘What is his **<u>son’s</u>** name? Surely you know!’ Meaning, so you will study and understand what his name is who is called Moses after the name of **<u>Metatron</u>**, the Minister of the Face.”

[Minkhat Eliyahu, quoting 'yalkut mishlei p.16]

በዚህ ስፍራ ሚንኻት ኤሊያሁ የተሰኘው የትንታኔ መጽሐፍ (commentary) ያልኩት ሚሽሌይ የተሰኘ ሚድራሽን በመጥቀስ፥ በዚህ ስፍራ ልጁ የተባለው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን በመስክረዋል። የአይሁድ ተንታኞች በታልሙዳቸውና በዞሃራቸው፥ የእግዚአብሔርን መልአክ "metatron/ሜታትሮን" ብለው ይጠሩታል። በነዚህ ምንጮቻቸው፥ ሜታትሮን/የእግዚአብሔር መልአክ "ያሕዌ" እንደሆነ፥ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ፥ የእግዚአብሔር ባህሪያት

በጠቅላላ እንዳሉት፥ የእስራኤል አምላክ እንደሆነ፥ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፥ ፍጥረትን ሁሉ እንደሚያስተዳድር ተናግረዋል። በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ልጅ ለወልድ የተባሉት ነገሮች በሙሉ፥ ለእርሱ ብለውታል። ከክርስትና በፊትም፥ ክርስትና ከተጀመረ በኋላም፥ ይህ ሜታትሮን ሁለተኛው የመለኮት አካል እንደነበር ያምኑ ነበር። ነገር ግን ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ፥ ክርስትናን ለመቃወም ይህን እምነት አወገዙ። (ስለዚህ ተጨማሪ ማስረጃ ለማግኘት Two powers in heaven, by allen f. segal እና Two gods in heave, by peter shaffer ይመልከቱ) የጥንት አይሁዳውያን ነጠላዊያን (unitarians) አልነበሩምና። ብዙ ተንታኞቻቸው ልጅ የተባለው እስራኤል ነው ቢሉም፥ ይህኛው ተርጓሚ ግን የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን ተናግሯል።

"what is his name and what is his son's name- that he may **<u>know</u>** in his **<u>wisdom</u>**. If you know- you are Atiel, adam or his son, tell me the name of one of them who knew him. And the reason: he **<u>cannot know</u>** and there are **<u>no creatures who knew his wisdom</u>**."

[Ibn Ezra a commentary on Proves 30:3-4]

በዚህ ስፍራ ይህ አይሁዳዊ ተንታኝ፥ አጉር ለምን የእግዚአብሔርንና የልጁን ስም እንደጠየቀ ያብራራል። በእርሱ መሰረት አጉር የእግዚአብሔርና የልጁን ስም የጠየቀው፥ እግዚአብሔር በአጉርም ሆነ በየትኛውም ፍጡር ሊታወቅ የማይችል ጥበብ ስላለው ነው ይላል። ማለትም፥ አጉር አዳም ወይንም የአዳም ልጅ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ጥበብ አያውቀውም። ስለዚህ፥ ጥበቡን ስላላወቀ ስሙን ጠየቀ። ይህ የሆነው እግዚአብሔር በየትኛውም ፍጡር ሊታወቅ የማይችል ጥበብ ስላለው ነው ይለናል። ይህ አተረጓጎም በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ልጅ፥ መለኮት እንደሆነ በግልፅ ያስረዳል። ምክንያቱም አጉር የጠየቀው የእግዚአብሔርን ስም ብቻ ሳይሆን የልጁንም ስም ነው። ይህ ማለት ይህ ልጅም እንዲሁ በየትኛውም ፍጡር ሊታወቅ የማይችል ጥበብ አለው ማለት ነው። ማለትም፥ መለኮት ነው፤ ምክንያቱም ከመለኮት በቀር በየትኛውም ፍጡር የማይታወቅ ጥበብ ያለው የለምና። ይህኛውም አፈታት ልጅ የተባለው እስራኤል አለመሆኑን ያሳያል። ምክንያቱም እስራኤል በፍጡር የማይታወቅ ጥበብ የለውም። ሰዎች ናቸው፥ ስለዚህ ከእግዚአብሔር እኩል ስማቸው አይጠየቅም። ይህ እግዚአብሔር መለኮታዊ ልጅ እንዳለው በግልፅ የሚያሳይ ማስረጃ ነው።

➢ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ከብሉይ ኪዳን የምናቀርበው ሁለተኛው ማስረጃ፦

2. **<u>ዳንኤል 3:25-28</u>**

*"እርሱም። እነሆ፥ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ፤ ምንም አላቈሰላቸውም፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን **<u>ልጅ</u>** ይመስላል ብሎ መለሰ።" (ትንቢተ*

*ዳንኤል 3:25)*

በዚህ ስፍራ እጅግ አስደናቂና በጣም ታዋቂ የሆነን ታሪክ እናነባለን። በንጉስ ኢዮአቄም ዘመን የነበረው የእስራኤል መንግስት ፈርሶ ባቢሎናውያን ምድሪቱን በተቆጣጠሩ ግዜ ብዙ አይሁዳውያን ምርኮኞችን ወደ ባቢሎን አፍልሰው ነበር። ከምርኮኞቹ መካከል አራት በጥበብና በእውቀት የተሻሉ ዳንኤል፥ አናንያ፥ ሚሳይልና አዛሪያ የተባሉ ወጣቶች አሉበት (ዳን 1:6)

እነዚህ ወጣቶች ምንም እንኳ በምርኮ ሀገር ቢገኙም ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር በቀር የባቢሎናውያንን ጣዖታት አናመልክም ብለው ጸኑ። እነዚህ ወጣቶች ከአምላካቸው በቀር ማንንም አናመልክም ብለው መከራን መቀበላቸው የመጽሐፉ ጭብጥ ነው።

በዳን 3 ላይም የምንመለከተው ክስተት ይህ ነው። ንጉሱ ናቡከደነፆር ቁመቱ ስልሳ ክንድ የሚሆን አንድ የወርቅ ጣዖትን ካሰራ በኋላ በግዛቱ ሁሉ የሚገኙ ሕዝቦች ያንን የወርቅ ሀውልት እንዲያመልኩ ያዛል። ይህንንም የማይፈጽም፤ በእቶን እሳት ውስጥ በመጣል እንደሚቀጣ ይደነግጋል

ነገር ግን ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጎ ንጉሱ ላቆመው ሀውልት ሳይሰግዱ ይቀራሉ። በዚህም ምክንያት ወደ ንጉሱ ቀርበው እርሱ ያሰራውን ሀውልት እንዲያመልኩ ሲጠይቃቸው፥ ቢሞቱ እንኳ የእርሱን አማልክት እንደማያመልኩ ይነግሩታል።

► በዚህም ግዜ ንጉሱ በቁጣ የእቶኑን እሳት ሰባት እጥፍ ካደረገው በኋላ፥ ወደዚያ እንዲጣሉ አደረገ። ይህንን ግዜ ነው ከሶስቱ አይሁዳውያን ጋር የነበረውን አራተኛውን ሰው ያየው

*"እርሱም። እነሆ፥ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ፤ ምንም አላቈሰላቸውም፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን **ልጅ** ይመስላል ብሎ መለሰ።" (ትንቢተ ዳንኤል 3:25)*

ንጉሱ ይህ ከእነርሱ ጋር የነበረው አራተኛው ሰው፥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በግልጽ መስክሯል። በተጨማሪ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ በማለት የጠራው መልአኩን እንደሆነም ተናግሯል

*"ናቡከደነፆርም መልሶ። **መልአኩን የላከ**፥ ከአምላካቸውም በቀር ማንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የንጉሡንም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን ያዳነ፥ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎም አምላክ ይባረክ።" (ትንቢተ ዳንኤል 3:28)*

ስለዚህ ይህ ክፍል በግልጽ የእግዚአብሔር መልአክ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያስተምር ክፍል ነው ማለት ነው።

► በዚህ ክፍል ላይ የሚነሱትን የተወሰኑ ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክር

1. **<u>በዚህ ስፍራ የተገለጠው መልአክ የቃል ኪዳኑ መልአክ መሆኑን በምን እናውቃለን?</u>**

ይህንን ክፍል በተመለከተ ከሚነሱት ጥያቄዎች መካከል፥ ይህ መልአክ "እግዚአብሔር ነኝ፥ አምላኩኝ" የሚለው መልአክ መሆኑን በምን እናውቃለን ነው። ምክንያቱም ፍጡራን መናፍስት ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋልና (ኢዮ 1:6 ኢዮ 2:1)

አዎ፥ ፍጡራን መናፍስት የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋል። ሁሉም ንቁዕ-ፍጥረታት የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። የፈጠራቸውና የሚያኖራቸው እርሱ ነውና በዚያ ረገድ አባታቸው ነው። መላእክትም እንዲሁ እግዚአብሔር በቀጥታ ስለፈጠራቸው (ዘፍ 2:1 ነህ 9:6 ሕዝ 28:13) የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።

ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ስም (መለኮት) በውስጡ ያለ አንዱ መልእክተኛ/መልአክ ፍጡር አይደለም። ያለና የነበረ ነው (ዘጽ 3:2/3:14) የእግዚአብሔር መለኮት በውስጡ አለ (ዘጽ 23:21) በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ባህርይ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር በህላዌው የሆነውን ነገር በሙሉ እርሱም ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር ደግሞ መጀመሪያና መጨረሻ አልባ ስለሆነ (ኢሳ 44:9) መልአኩም እንዲሁ ዘላለማዊ ነው ማለት ነው።

ይህ መልአክ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ባህርይ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች ያደርጋል። ለምሳሌ፦

| | **እግዚአብሔር** | **መልአኩ** |
|---|---|---|
| ➢ ሀጢአትን ይቅር አለማለት | "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ **<u>እግዚአብሔር</u>** ስሙን በከንቱ የሚጠራውን **<u>ከበደል አያነጻውምና</u>**። " (ኦሪት ዘጸአት 20:7) | "በፊቱ ተጠንቀቁ፥ ቃሉንም አድምጡ፤ ስሜም በእርሱ ስለ ሆነ **<u>ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና</u>** አታስመርሩት።" (ኦሪት ዘጸአት 23:21) |
| ➢ ሁሉን መመልከት | **"<u>ዓይኖቹ</u>** በሰው መንገድ ላይ ናቸው፥ እርምጃውንም **<u>ሁሉ ያያ</u>**ል።" (መጽሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ 34:21) | "እርስዋም ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ስም **<u>ኤልሮኢ</u>** ብላ ጠራች፤ **<u>የሚያየኝን</u>** በውኑ እዚህ ደግሞ አየሁትን? ብላለችና።" (ኦሪት ዘፍጥረት 16:13) |

| | | |
|---|---|---|
| ➢ በሁሉ ስፍራ መገኘት | "ሰው በስውር ቢሸሽግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ **<u>የሞላሁ</u>** እኔ አይደለሁምን? **<u>ይላል እግዚአብሔር</u>**።" (ትንቢተ ኤርምያስ 23:24) | "የእግዚአብሔር **<u>መልአክ</u>** በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ **<u>ይሰፍራል</u>**፥ ያድናቸውማል።" (መዝሙረ ዳዊት 34:7) |
| ➢ ሀጢያትን ይቅር ማለት | "ዳዊትም ናታንን። እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን። **<u>እግዚአብሔር</u>** ደግሞ **<u>ኃጢአትህን አርቆልሃል</u>**፤ አትሞትም።" (መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 12:13) | "**<u>መልአኩም</u>** ከፊቱ ቆመው የነበሩትን፣ ያደፉ ልብሶቹን አውልቁለት አላቸው። ኢያሱንም፣ "እነሆ፤ **<u>ኀጢአትህን ከአንተ አስወግጃለሁ</u>**፤ ጥሩ ልብስም አለብስሃለሁ አለው። (ዘካርያስ 3፥4) (አዲሱ መ.ት) |
| ➢ ታላቅ ሕዝብ ማድረግ | "አለውም። የአባቶችህ አምላክ **<u>እግዚአብሔር</u>** እኔ ነኝ፤ ወደ ግብፅ መውረድ አትፍራ፥ **<u>በዚያ ትልቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና</u>**።" (ኦሪት ዘፍጥረት 46:3) | "17፤ እግዚአብሔርም የብላቴናውን ድምፅ ሰማ፤ የእግዚአብሔርም **<u>መልአክ</u>** ከሰማይ አጋርን እንዲህ ሲል ጠራት። 18፤ ተነሺ፥ ብላቴናውንም አንሺ፥ እጅሽንም በእርሱ አጽኚው፤ **<u>ትልቅ ሕዝብ አደርገዋለሁና</u>**።" (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 21:17-18) |
| ➢ እስራኤልን ከግብፅ ማውጣት | "**<u>ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ</u>** እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ።" (ኦሪት ዘጸአት 20:2) | "የእግዚአብሔርም **<u>መልአክ</u>** ከጌልገላ ወደ ቦኪም ወጥቶ እንዲህ አለ። **<u>እኔ ከግብፅ አውጥቻችኋለሁ</u>**፥ ለአባቶቻችሁም ወደ ማልሁላቸው ምድር አግብቻችኋለሁ፤" (መጽሐፈ መሳፍንት 2:1) |

| | | |
|---|---|---|
| ➢ መስዋዕትን መቀበል | "**<u>እሳትም</u>** ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጣ፥ **<u>በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ስቡንም በላ</u>**፤ ሕዝቡም ሁሉ አይተው እልል አሉ፥ በግምባራቸውም ወደቁ።" (ኦሪት ዘሌዋውያን 9:24) | "የእግዚአብሔርም **<u>መልአክ</u>** በእጁ ያለውን የበትሩን ጫፍ ዘርግቶ ሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ አስነካ፤ **<u>እሳትም ከድንጋዩ ውስጥ ወጥቶ ሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ በላ</u>**። የእግዚአብሔርም መልአክ ከዓይኑ ተሰወረ።" (መጽሐፈ መሳፍንት 6:21) |
| ➢ እስራኤልን ከባርነት ማዳን | "እስራኤል ሆይ፥ ምስጉን ነህ፤ **<u>በእግዚአብሔር የዳነ</u>** ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው?" (ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 33:29) | "በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ **<u>የፊቱም መልአክ አዳናቸው</u>**፤ በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፥ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 63:9) |
| ➢ ሕዝቡን በምድረ በዳ መጠበቅ | "10፤ በምድረ በዳ በጥማት፥ የነፋስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው፤ ከበበው ተጠነቀቀለትም፤ እንደ ዓይን ብሌን **<u>ጠበቀው</u>**።" (ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 32:10) | "በመንገድ **<u>ይጠብቅህ</u>** ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ፥ እነሆ፥ እኔ **<u>መልአክን</u>** በፊትህ እሰድዳለሁ።" (ኦሪት ዘጸአት 23:20) |
| ➢ ከሕዝቡ ፊት መሄድ | "**<u>በፊታችሁ የሚሄደው አምላካችሁ እግዚአብሔር</u>**፥ እናንተ ስታዩ በግብፅና በምድረ በዳ እንዳደረገላችሁ ሁሉ፥ ስለ እናንተ ይዋጋል፤" (ኦሪት ዘዳግም 1:30) | "**<u>መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና</u>**፥ ወደ አሞራውያንም ወደ ኬጢያውያንም ወደ ፌርዛውያንም ወደ ከነዓናውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳውያንም ያገባሃል፤ እኔም አጠፋቸዋለሁ።" (ኦሪት ዘጸአት 23:23) |

| | | |
|---|---|---|
| ➢ እስራኤልን ወደ አሕዛቡ ምድር ማግባት | "**<u>እግዚአብሔርም</u>** ለአንተ ይሰጣት ዘንድ ለአባቶችህ ወደ ማለላቸው፥ ወተትና ማር ወደምታፈስስ ምድር፥ ወደ **<u>ከነዓናውያን</u>** ወደ **<u>ኬጢያውያንም</u>** ወደ **<u>አሞራውያንም</u>** ወደ **<u>ኤዊያውያንም</u>** ወደ **<u>ኢያቡሳውያንም</u>** ምድር **<u>ባገባህ</u>** ጊዜ ይህችን አምልኮ በዚህ ወር ታደርጋለህ።" (ኦሪት ዘጸአት 13:5) | "**<u>መልአኬ</u>** በፊትህ ይሄዳልና፥ ወደ **<u>አሞራውያንም</u>** ወደ **<u>ኬጢያውያንም</u>** ወደ **<u>ፌርዛውያንም</u>** ወደ **<u>ከነዓናውያንም</u>** ወደ **<u>ኤዊያውያንም</u>** ወደ **<u>ኢያቡሳውያንም</u> <u>ያገባሃል</u>**፤ እኔም አጠፋቸዋለሁ።" (ኦሪት ዘጸአት 23:23) |
| ➢ የቃል ኪዳኑን ምድር ማውረስ | "ሳይጎድልህ እንጀራን ወደምትበላባት አንዳችም ወደማታጣባት ምድር፥ ድንጋይዋ ብረት ወደ ሆነ፥ ከተራራዋም መዳብ ወደሚማስባት **<u>ምድር ያገባሃል</u>**።" (ኦሪት ዘዳግም 8:9) | "በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ **<u>ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ</u>** ዘንድ፥ እነሆ፥ እኔ **<u>መልአክን</u>** በፊትህ እሰድዳለሁ።" (ኦሪት ዘጸአት 23:20) |
| ➢ የመሰማት ስልጣን | "አሁንም **<u>ቃሌን በእውነት ብትሰሙ</u>** ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ፤" (ኦሪት ዘጸአት 19:5) | "አንተ ግን **<u>ቃሉን ብትሰማ</u>**፥ ያልሁህንም ሁሉ ብታደርግ፥ ጠላቶችህን እጣላቸዋለሁ፥ የሚያስጨንቁህንም አስጨንቃቸዋለሁ።" (ኦሪት ዘጸአት 23:22) |
| ➢ ዘርን ማብዛት | "በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፥ **<u>ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ</u>**፤ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤" (ኦሪት ዘፍጥረት 22:17) | "የእግዚአብሔር **<u>መልአክም</u>**። **<u>ዘርሽን እጅግ አበዛለሁ</u>**፥ ከብዛቱም የተነሣ **<u>አይቆጠርም</u>** አላት።" (ኦሪት ዘፍጥረት 16:10) |

| | | |
|---|---|---|
| ➢ የመባረክ ስልጣን | "ሰማይንና ምድርን የሠራ **<u>እግዚአብሔር</u>** ከጽዮን **<u>ይባርክህ</u>**።" (መዝሙረ ዳዊት 134:3) | "ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ **<u>መልአክ</u>**፥ **<u>እርሱ</u>** እነዚህን ብላቴኖች **<u>ይባርክ</u>**፤ ስሜም የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅም ስም በእነርሱ ይጠራ፤ በምድርም መካከል ይብዙ።" (ኦሪት ዘፍጥረት 48:16) |
| ➢ የሠራዊት አለቃ መሆን | "እስከ **<u>ሠራዊትም አለቃ</u>** ድረስ ራሱን ታላቅ አደረገ፤ ከእርሱም የተነሣ የዘወትሩ መሥዋዕት ተሻረ፥ የመቅደሱም ስፍራ ፈረሰ።" (ትንቢተ ዳንኤል 8:11) | "**<u>የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ</u>** ኢያሱን። አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።" (መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 5:15) |
| ➢ ከመታወቅ በላይ መሆን | "እነሆ፥ **<u>እግዚአብሔር</u>** ታላቅ ነው፥ እኛም **<u>አናውቀውም</u>**።" (መጽሐፈ ኢዮብ 36:26) | "የእግዚአብሔርም **<u>መልአክ</u>**። **<u>ስሜ ድንቅ ነውና</u>** ለምን ትጠይቃለህ? አለው።" (መጽሐፈ መሳፍንት 13:18) |
| ➢ በደልን መመልከት | "እንዲሁም ንጉሡ ኢዮአስ ዮዳሄ ያደረገለትን ቸርነት አላሰበም፥ ልጁንም ዘካርያስን አስገደለው፤ እርሱም ሲሞት። **<u>እግዚአብሔር ይየው</u>**፥ ይፈልገውም አለ።" (መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 24:22) | "የእግዚአብሔርም **<u>መልአክ</u>** በሕልም። ያዕቆብ ሆይ አለኝ፤ እኔም። እነሆኝ አልሁት። 12፤ እንዲህም አለኝ። ዓይንህን አቅንተህ እይ፤ በበጎችና በፍየሎች ላይ የሚንጠላጠሉት የበጎችና የፍየሎች አውራዎች ሽመልመሌ መሳዮችና ዝንጕርጕሮች ነቁጣ ያለባቸውም ናቸው፤ **<u>ላባ በአንተ ላይ የሚያደርገውን ሁሉ አይቼአለሁና</u>**።" (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 31:11-12) |

| | | |
|---|---|---|
| ➢ ሁሉን ማወቅ | "**<u>ጌታችን</u>** ታላቅ ነው፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥ **<u>ለጥበቡም ቍጥር የለውም</u>**።" (መዝሙረ ዳዊት 147:5) | "ባሪያህ ኢዮአብ የዚህ ነገር መልክ እንዲለወጥ አደረገ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር **<u>መልአክ</u>** ጠቢብ **<u>እንደ</u>** ሆነ፥ አንተም ጌታዬ **<u>በምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ታውቅ ዘንድ</u>** ጠቢብ ነህ አለች።" (መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 14:20) |

እነዚህ ባህሪያት በሙሉ የመለኮት ብቸኛ ባህሪያት ናቸው። ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የእነዚህ ባህሪያት ባለቤት ሊሆን አይችልም። መልአኩ ግን የእግዚአብሔር ስም (መለኮት) በውስጡ ስላለ፤ እነዚህ ባህሪያት ኖሩት

► ይህንን ሀቅ ከተረዳን ዘንድ፥ በዳን 3 ሶስቱን አይሁዳውያን ለማዳን የተገለጠው መልአክ ማን እንደሆነ ማረጋገጥ እንችላለን። ምክንያቱም ይህ መልአክ፥ እግዚአብሔር ብቻ አደርገዋለሁ ያለውን ነገር ነው ያደረገው

*"በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ **<u>ከአንተ ጋር</u>** እሆናለሁ፥ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ **<u>በእሳትም</u>** ውስጥ በሄድህ ጊዜ **<u>አትቃጠልም</u>**፥ ነበልባሉም **<u>አይፈጅህም</u>**።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 43:2)*

በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳያስ አማካኝነት ለእስራኤል የአብሮነት ቃል ኪዳን ሲገባ እንመለከታለን። የእርሱ እንደሆኑ እና በእሳት ውስጥ ቢያልፉ እንኳ ከእነርሱ ጋር ስለሆነ እሳቱ እንደማያቃጥላቸው ቃል ይገባላቸዋል።

ይህንን አይነት ቃል የገባው እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን፥ የትኛውም ፍጡር እንዲህ አደርጋለሁ ብሎ አያውቅም። ስለዚህ የመለኮት ብቸኛ ባህርይ ነው ማለት ነው። የትኛውም ፍጡር ይህንን ሊያደርግ አይችልም ማለት ነው

◆ ነገር ግን መልአኩ ያ እግዚአብሔር ብቻ አደርገዋለሁ ያለውን ነገር አደረገ። ከእነርሱ ጋር ስለነበር እሳቱ አላቃጠላቸውም። አራተኛ ሰው በመሆን አብሯቸው የነበረው እርሱ ነውና። (ዳን 3:25) እግዚአብሔር ብቻ አደርገዋለሁ ያለውን ተግባር በማድረጉ፥ እርሱ ያ ከእግዚአብሔር ጋር በመለኮት አንድ የሆነው መልአክ መሆኑን ያረጋግጣል። ከመለኮት በቀር ማንም ሊያደርገው የማይችለውን ነገር አድርጓልና።

2. **<u>ንጉሱ የእግዚአብሔር ልጅ ሳይሆን ያለው "የአማልክት ልጅ" ነው</u>**

ሌላኛው ጥያቄ "ንጉሱ አራተኛው ሰው የአማልክት ልጅ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ ነው አላለም። ጣዖት አምላኪ አሕዛብ ስለሆነ፤ የእርሱ አማልክት ልጅ ማለቱ ነው" የሚሉ ወገኖች አሉ

► ይህ ፈጽሞ ስህተት ነው። ንጉሱ የአማልክት ልጅ ሲል፥ የእነርሱን አምላክ እግዚአብሔርን እንጂ የእርሱን አማልክት ማለቱ አይደለም። ምክነያቶቹን እነሆ፦

1. ንጉሱ ወጣቶቹን ወደ እሳቱ ያስጣለው የእርሱን አማልክት አናመልክም በማለታቸው ነው

ንጉሱ የወርቅ ሀውልቱን አሰርቶ ከጨረሰ በኋላ መኳንንትና ሹማምንትን ሰብስቦ ለዚያ ሀውልት እንዲሰግዱ ያዛል። የመለከትና የእምቢልታ ድምጽ ሲሰማ ለጣዖቱ የማይሰግድ ሁሉ በእቶን እሳት ውስጥ እንደሚጣልም ያሳውቃል። ነገር ግን እነዚህ ወጣቶች ሳይሰግዱ ይቀራሉ

ንጉሱም አስጠርቷቸው ለአምላኩ የማይሰግዱ ከሆነ፥ በእቶን እሳት ውስጥ እንደሚጣሉና፥ የትኛውም አምላክ ሊያድናቸው እንደማይችል ይነግራቸዋል (ዳን 3:14-15)። እነርሱ ግን ጸንተው የእርሱን አማልክት እንደማያመልኩ ይነግሩታል፦

*"ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ **አማልክትህን እንዳናመልክ** ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት።" (ትንቢተ ዳንኤል 3:18)*

ስለዚህ ወጣቶቹ ወደ እሳቱ የተጣሉት፥ የንጉሱን አማልክት አናመልክም በማለታቸው ነው።

♦ታዲያ ንጉሱ ከእሳቱ ሲድኑ ሲያይ፥ እንዴት **የኔ አማልክት** አዳናቸው ሊል ይችላል? ወደ እሳቱ የገቡት የእርሱን አማልክት አናመልክም በማለታቸው ሆኖ ሳለ?! የእርሱን አማልክት አናመልክም ብለው ወደ እሳቱ መጣላቸው፥ ያዳናቸው ያ አናመልከውም ያሉት አማልክት ሊሆን እንደማይችል ግልፅ ያደርጋል።

2. ወጣቶቹ ከእሳቱ የሚያድናቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑን ቀድመው መናገራቸው

ንጉሱ የእርሱን አማልክት ካላመለኩ፥ ወደ እሳቱ እንደሚጥላቸው ሲነግራቸው፥ ወጣቶቹ አምላካቸው እግዚአብሔር ከእሳቱ እንደሚያድናቸው ይነግሩታል

*"**የምናመልከው አምላካችን** ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን **ያድነን** ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም **ያድነናል**፥ ንጉሥ ሆይ!" (ትንቢተ ዳንኤል 3:17)*

ስለዚህ ወጣቶቹ ወደ እሳቱ ከመግባታቸው አስቀድመው፥ ከእሳቱ የሚያድናቸው የራሳቸው አምላክ መሆኑን ነግረውታል። የሚያድናቸው እግዚአብሔር ነው

♦ታዲያ ንጉሱ ከእሳቱ ሲድኑ ሲያይ፥ እንዴት **የኔ አማልክት** ልጅ አዳናቸው ሊል ይችላል? የሚያድናቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑን አስቀድመው ነግረውት ሳለ?! የሚያድናቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑ አስቀድመው መናገራቸው፥ ያዳናቸው የእስራኤልን አምላክ ያልሆነ ሌላ

አማልክት ሳይሆን ራሱ የእስራኤል አምላክ መሆኑን ግልፅ ያደርጋል።

3. ንጉሱ በራሱ አንደበት ያዳናቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑን መመስከሩ

ወጣቶቹ ከእሳቱ ከዳኑ በኋላ፥ ንጉሱ በራሱ አንደበት ያዳናቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑን እንዲህ በማለት መስክሯል

*"ናቡከደነፆርም መልሶ። መልአኩን የላከ፥ **<u>ከአምላካቸውም በቀር ማንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ</u>** ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የንጉሡንም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን **<u>ያዳነ</u>**፥ **<u>የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎም</u>** **<u>አምላክ</u>** ይባረክ።" (ትንቢተ ዳንኤል 3:28)*

♦ታዲያ ንጉሱ እንዴት **<u>የኔ አማልክት</u>** ልጅ አዳናቸው ሊል ይችላል? ያዳናቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑን በራሱ አንደበት እየመሰከረ?! አዳኛቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑን መመስከሩ፥ በእርግጥም "**<u>የአማልክት ልጅ</u>**" ሲል የሌላ አምላክ ልጅ ሳይሆን፥ የራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ማለቱ እንደሆነ በግልፅ ያሳያል።

4. ንጉሱ ከእነርሱ አምላክ በቀር ሌላ አምላክ እንዲህ ሊያድን እንደማይችል መመስከሩ

ንጉሱ ያዳናቸው የእነርሱ አምላክ መሆኑን ከመመስከር ባሻገር፥ ከእነርሱ አምላክ በቀር እንዲህ ሊያድን የሚችል ሌላ አምላክ እንደሌለ መስክሯል

*"እኔም **<u>እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና በሲድራቅና በሚሳቅ በአብደናጎም አምላክ</u>** ላይ የስድብን ነገር የሚናገር ወገንና ሕዝብ በልዩ ልዩም ቋንቋ የሚናገሩ ይቈረጣሉ፥ ቤቶቻቸውም የጕድፍ መጣያ ይደረጋሉ ብዬ አዝዣለሁ አለ።" (ትንቢተ ዳንኤል 3:29)*

♦ይገርማል! ከእነርሱ አምላክ በቀር እንዲህ የሚያድን ሌላ አምላክ እንደሌለ የመሰከረ ንጉስ እንዴት ነው ያዳናቸው **<u>የኔ አማልክት</u>** ነው ሊል የሚችለው?! ከእነርሱ አምላክ በቀር እንዲህ የሚያድን እንደሌለ መመስከሩ፥ "**<u>የአማልክት ልጅ</u>**" ሲል ያዳናቸው የእስራኤል አምላክ ልጅ ማለቱ እንጂ የሌላ አማልክት ልጅ አለመሆኑን በማያሻማ መልኩ ያሳያል።

ስለዚህ ንጉሱ "የአማልክት ልጅ" ሲል እየተናገረ የነበረው ስለ እነርሱ አምላክ ነው። በዙሪያው ባለው አውድ መሰረት፥ የእነርሱ አምላክ ልጅ ማለቱ እንጂ የእርሱ አማልክት ልጅ ማለቱ ሊሆን አይችልም።

➢ ታዲያ ለምን "የአማልክት" ብሎ ቃሉን በብዜት ተጠቀመ?

በብሉይ ኪዳን በእስራኤልና በመካከለኛው ምስራቅ አምላክን በብዜት መጥራት የተለመደ ነው። ስለ አንዱ አምላክ እየተናገሩ "አማልክት" ማለት ይቻላል። ይህ የሰዋሰው አጠቃቀም

ነው። ለምሳሌ

*"**<u>አምላክ</u>** ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘላለም ነው፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው።" (መዝሙረ ዳዊት 45:6)*

በዚህ ስፍራ አምላክ የሚለው ቃል "ኤሎሂም" ሲሆን በቀጥታ ሲተረጎም "አማልክት" ማለት ነው። ነገር ግን ክፍሉ የሚናገረው ስለ መሢሑ ስለ ክርስቶስ ነው (ዕብ 1:8) በሰዋሰው ብዙ (plural) ቢሆንም አንድ አካልን ለማመልከት ሊውል ይችላል

ሌላ ምሳሌ

*"እግዚአብሔርም **<u>ሙሴን</u>** አለው። እይ፥ እኔ ለፈርዖን **<u>አምላክ</u>** አድርጌሃለሁ፤ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል።" (ኦሪት ዘጸአት 7:1)*

በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ሙሴን ለፈርዖን አምላክ አድርጌያለሁ ሲለው እንመለከታለን። አሁንም አምላክ የሚለው ቃል "ኤሎሂም" ነው። በሰዋሰው ደረጃ ብዙ (plural) ሲሆን በቀጥታ ሲተረጎም "አማልክት" ማለት ነው። ነገር ግን የዋለው ለሙሴ ነው

አምላክ/አማልክት የሚለው ቃል ለብዙ አማልክት ይሁን ለአንዱ አምላክ መዋሉን የምናረጋግጠው በአውዱ ነው። በዳን 3 አውድ ደግሞ አማልክት ተብሎ የተጠራው እግዚአብሔር ነው። ያዳነው፥ መልአኩን የላከው፥ እርሱ ነውና። ስለዚህ አምላክ ተብሎ ነው መታየት ያለበት

► ይህንንም ሀቅ የተረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚያን "እግዚአብሔር" ወይንም "God" ብለው ተርጉመውታል

“He answered and said, Lo, I see four men loose, walking in the midst of the fire, and they have no hurt; and the form of the fourth is like **<u>the Son of God</u>**.”

-Daniel 3:25 (KJV)

“And the king said, But I see four men loose, and walking in the midst of the fire, and there has no harm happened to them; and the appearance of the fourth is like **<u>the Son of God</u>**.”

-Dan 3:25 (ABC)

“He answered and said, See, I see four men loose, walking in the middle of the fire, and they have no hurt; and the form of the fourth is like **<u>the Son of</u>**

**God**."

-Dan 3:25 (AKJV)

3. **ንጉሡ ለምን የአማልክትን ልጅ "ይመስላል" አለ?**

ሌላኛው ጥያቄ፥ ንጉሱ ለምን የአማልክት ልጅ ይመስላል አለ የሚል ነው። በትክክል የመልአኩን/መልእክተኝነቱን የእግዚአብሔር ልጅነት መናገር ቢፈልግ ኖሮ ይመስላል ባላለ ነበር የሚል ነው። ይህም ፈጽሞ የተሳሳተ አመለካከት ነው። ምክንያቱም ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ሲገለጥ፥ ሰዎች እርሱ መሆኑን አይተው የሚያውቁበት የራሱ መልክ አለው። በፊታቸው የተገለጠው ተራ ሰው ሳይሆን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ (supernatural) አካል መሆኑን የሚያመለክት መልክ አለው። ስለዚህ ሰዎች የተገለጠላቸውን ሰው ሲያዩት "የእግዚአብሔር መልአክን" ይመስላል ይላሉ። ምክንያቱም መልኩ የተራ ሰው መልክ አይደለምና። ለምሳሌ፦

*"ሴቲቱም ወደ ባልዋ መጥታ። አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ፥ **መልኩም እንደ** እግዚአብሔር **መልአክ** እጅግ የሚያስደነግጥ ነበረ፤ ከወዴትም እንደ መጣ አልጠየቅሁትም፥ እርሱም ስሙን አልነገረኝም።" (መጽሐፈ መሳፍንት 13:6)*

"6 Then the woman came and told her husband, saying, A man of God came unto me, and **his countenance** was **like the countenance of an angel of God**, very terrible: but I asked him not whence he was, neither told he me his name:" (Judges 13:6)

በዚህ ስፍራ የማኑሄ ሚስት የእግዚአብሔርን መልአክ አይታ የተናገረችውን ነገር እንመለከታለን። የእግዚአብሔር መልአክ በሰው አምሳል ከተገለጠላት በኋላ (መሳ 13:3) ወደ ባሏ ወደ ማኑሄ ትሄድና ይህን ነገር ትነግረዋለች። አንድ ሰው እንደተገለጠላትና፥ ያም ሰው መልኩ እንደ እግዚአብሔር መልአክ የሆነና የሚያስደነግጥ እንደነበር ትነግረዋለች። የማኑሄ ሚስት "መልኩ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነበር" ማለቷ፥ ስለ እግዚአብሔር መልአክ የቀደመ እውቀት እንደነበራት ያሳያል። የቀደመ እውቀት ስለነበራት እርሱን ስታየው፥ ከእርሱ ጋር relate ልታደርግ ችላለች። "መልኩ **እንደ** እግዚአብሔር መልአክ ነው" ማለቷ የተገለጠላት የእግዚአብሔር መልአክ አይደለም አያስብልም። መልኩ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ይመስላል ማለቷ እርሱን አይታው እንዳወቀችው ያሳያል እንጂ፥ የተገለጠላት መልአኩ አለመሆኑን አያሳይም። የተገጠላት እርሱ ነውና

ስለዚህ በዳን 3:25-28 ላይም፥ የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል ሲል ልክ እንደ ማኑሄ ሚስት እርሱን ያወቀበት መልኩ ነው። ንጉሱ ስለ እግዚአብሔር መልአክ የቀደመ እውቀት አለው። የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፥ ለቅዱሳን እንደሚታይ፥ እስራኤልን ለማዳን እንደሚገለጥ፥ በሰው

አምሳል እንደሚመጣ ያውቃል። ስለዚህ ከሶስቱ እስራኤላውያን ጋር በእሳቱ ውስጥ አራተኛ ሰው ሲያይ፥ ልክ እንደ ማኑሄ ሚስት መልኩ የእግዚአብሔር መልአክን እንደሚመስል ተረዳ። ስለዚህ "አራተኛው ሰው የአማልክትን ልጅ (like the Son of God) ይመስላል አለ። ስለ እርሱ የቀደመ እውቀት ስላለው፥ እርሱን ባየበት ሰዓት መልአኩ መሆኑን አወቀ። ንጉሱ ልጅ እና መልአክ/መልእክተኛ የሚሉትን ስሞች የሚጠቀማቸው በተቀያያሪነት ነው። ምክንያቱም በቁ.25 ላይ "ልጅ" ያለውን በቁ.28 ላይ "መልአክ" ብሎታል። ስለዚህ መልኩ የእግዚአብሔርን ልጅ ይመስላል ሲል፥ የእግዚአብሔርን መልአክ ይመስላል ማለቱ ነው። ነገር ግን፥ ልክ እንደ ማኑሄ ሚስት እርሱን አይቶት ማን እንደሆነ ማወቁን የገለጸው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በመመስከር ነው።

"25 He answered and said, Lo, I see four men loose, walking in the midst of the fire, and they have no hurt; and **the form** of the fourth is **like the Son of God**." (Daniel 3:25)

✏ የተለያዩ የመጽሐፍ  ቅዱስ ተንታኞች በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተለውን ብለዋል፦

"His **countenance** she could describe; it was very awful: he had such a majesty in his looks, such a sparkling eye, such a shining face, so powerfully commanding reverence and respect, that according to the idea she had of an **angel** he had the very countenance of one."

➢ (Mathew Henry Bible Commentary, Judges 13:6)

"and his **countenance** was like the countenance of an **angel of God**, very terrible; for though she might never have seen an angel, yet it being a common notion that angels were very illustrious, of a beautiful form and of a shining countenance, and very majestic, she compares the man she saw to one; for by being "very terrible," is not meant that he was frightful, and struck her with horror, but venerable and majestic, which filled her with admiration"

➢ (Gill's Exposition of the Entire Bible, Judges 13:6)

"Though Manoah's wife had never seen an **angel** before, yet she might well say this, as it was a prevailing opinion among all people, that celestial beings were more excellent in their nature than mankind, and bore an extraordinary majesty in their **countenances**, which struck the human

beholder with awe and admiration."

➢ (Benson Commentary, Judges 13:6)

"**the angel** in whom the invisible God reveals himself to men. The woman therefore imagined the person who appeared to her to have been a prophet, whose majestic **appearance**, however, had produced the impression that he was a superior being; consequently she had not ventured to ask him either his name or where he came from."

➢ (Keil and Delitzsch Biblical Commentary on the Old Testament, Judges 13:6)

የአይሁድ ተንታኞችም እንዲሁ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ሰጥተዋል፦

"Who saw him in the form of a man, and decreed that he was a man of God,whether because of the prophecy and destiny he said to her, and whether **the radiance of his form** and **the majesty of his face,** as she said and looked like the **angel** of God, that her delusion in the matter of the angel to be the shape of his face is a **terrible and wonderful** thing"

➢ (Arbabnel, commentary on Judges 13:6)

♦እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች እንደመሰከሩት፥ የማኑሄ ሚስት የመልአኩን መልክ ስትመለከተው ማን እንደሆነ አውቃለች። ይህ የእግዚአብሔር መልአክ ሲገለጥ፥ እርሱ መሆኑን የሚታወቅበት መልክ እንዳለው ያረጋግጣል። ለዚያም ነው የማኑሄ ሚስት መልአኩን ስትመለከተው እርሱ መሆኑን ያወቀችው። በዳን 3:25 ላይም ንገሡ "ይመስላል" ያለው በዚህ ምክንያት ነው። ናቡከደነጾር ያየው እርሷ ያየችውን መልክ ነውና።

4. **ንጉሱ መልአኩ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በምን አወቀ?**

ሌላኛው ጥያቄ ደግሞ፤ "ንጉሱ አሕዛብ ስለሆነ መልአኩ የእስራኤል አምላክ ልጅ መሆኑን ሊያውቅ አይችልም። ስለዚህ የእርሱ ምስክርነት ተቀባይነት የለውም" የሚል ነው

► ይህ የተሳሳተ እይታ ነው። በመጀመሪያ መልአኩ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ የተገለጸው በዚህ ስፍራ ብቻ አይደለም። በሌላም ቦታ መልአኩ መለኮታዊው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ተገልጿል (ምሳ 30:4) ሲቀጥል ንጉሱ ምንም እንኳ አሕዛብ ቢሆንም፥ ስለ እስራኤል አምላክ ትክክለኛ መረዳት እንደነበረው እንረዳለን

*"**ንጉሡም** ዳንኤልን። ይህን ምሥጢር ትገልጥ ዘንድ ተችሎሃልና በእውነት **አምላካችሁ የአማልክት አምላክ**፥ **የነገሥታትም ጌታ**፥ ምሥጢርም ገላጭ ነው ብሎ ተናገረው።" (ትንቢተ ዳንኤል 2:47)*

በዚህ ስፍራ ነቢዩ ዳንኤል የንጉሱን ሕልም ከነገረውና ከፈታለት በኋላ የተናገረውን ንግግር እንመለከታለን። የነ ዳንኤል አምላክ "የአማልክት አምላክና የነገስታት ጌታ" መሆኑን ይመሰክራል

እግዚአብሔር የአማልክት አምላክና የነገስታት ጌታ መሆኑ በኦሪት የተረጋገጠ እውነት ነው። ነገር ግን ንጉሱ ይህንን እውነት ሊያውቅ ቻለ። እንዴት?

*"16፤17፤ እንግዲህ **አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ**፥ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም፥ በፍርድ የማያደላ፥ መማለጃም የማይቀበል ነውና እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ፥ ክእንግዲህ ወዲህም አንገተ ደንዳና አትሁኑ።" (ኦሪት ዘዳግም 10:16-17)*

*"2፤ **የአማልክትን አምላክ** አመስግኑ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና። 3፤ **የጌቶችን ጌታ** አመስግኑ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤" (መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 136:2-3)*

*"**የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር፥ የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር** እርሱ አውቆታል፥ እስራኤልም ያውቀዋል፤ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀንና ተላልፈን እንደ ሆነ ዛሬ አታድነን፤" (መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 22:22)*

► ሌላው ፥ ንጉሱ በእሳቱ ውስጥ የነበረው አራተኛ ሰው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን መስክሯል (ዳን 3:28) ያ ሰው መልአኩ መሆኑን በምን አወቀ?

ንጉሱ ያ ሰው መልአኩ መሆኑን መመስከሩ ትክክል ነው። ምክንያቱም በሰው አምሳል ተገልጦ እግዚአብሔር ብቻ የሚያደርገውን ነገር የሚያደርገው እርሱ ነውና። (መሳ 6:19/ዘጽ 22:20 ኢያ 5:15/ዘጽ 3:5) አራተኛው ሰው ደግሞ ተገልጦ ያደረገው መለኮት ብቻ የሚያደርገውን ነው (ኢሳ 43:2) ስለዚህ ንጉሱ ትክክል ነበር ማለት ነው

በተጨማሪም፥ ንጉሱ እግዚአብሔር ለዘላለም እንደሚኖር፥ መንግስቱ ለልጅ ልጅ እንደሆነ፥ አሕዛብን እንደ ምናምን እንደሚቆጥር፥ በሰማይም በምድርም ፈቃዱን እንደሚያደርግ፥ እጁንም የሚከለክል እንደሌለ ተናግሯል።

*"34፤ ዘመኑም ከተፈጸመ በኋላ እኔ ናቡከደነፆር ዓይኔን ወደ ሰማይ አነሣሁ፥ አእምሮዬም ተመለሰልኝ፤ **ልዑሉንም** ባረክሁ፥ **ለዘላለምም የሚኖረውን አመሰገንሁ አከበርሁትም፤ ግዛቱ የዘላለም ግዛት ነውና፥ መንግሥቱም ለልጅ ልጅ ነውና። 35፤ በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ***

*<u>**ምናምን ይቈጠራሉ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፤ እጁንም የሚከለክላት ወይም። ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም።**</u>" (ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 4:33-34)*

እነዚህ ምስክርነቶች በሙሉ እውነት ከመሆናቸው ባሻገር፥ ነቢያት በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር የተናገሯቸው ነገሮች ናቸው። ንጉሱ ይህንን ሁሉ እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

*"<u>**ለዘላለም የሚኖር**</u> ስሙም ቅዱስ የሆነ፥ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል። የተዋረዱትን ሰዎች መንፈስ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠውንም ልብ ሕያው አደርግ ዘንድ፥ የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ስፍራ እቀመጣለሁ።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 57:15)*

*"አቤቱ፥ አንተ ለዘላለም ትኖራለህ፤ <u>**ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው**</u>።" (ሰቆቃው ኤርምያስ 5:19)*

*"እነሆ፥ <u>**አሕዛብ**</u> <u>**በገንቦ እንዳለች ጠብታ ናቸው፥ በሚዛንም እንዳለ ትንሽ ትቢያ ተቈጥረዋል**</u>፤ እነሆ፥ ደሴቶችን እንደ ቀላል ነገር ያነሣል።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 40:15)*

*"አምላካችንስ በላይ በሰማይ ነው፤ <u>**በሰማይም በምድርም የፈቀደውን ሁሉ አደረገ።**</u>" (መዝሙረ ዳዊት 115:3)*

*"ከጥንት ጀምሮ እኔ ነኝ <u>**ከእጄም**</u> የሚያመልጥ የለም፤ እሠራለሁ፥ <u>**የሚከለክልስ ማን ነው**</u>?" (ትንቢተ ኢሳይያስ 43:13)*

ስለዚህ፥ ንጉሱ አሕዛብ ስለሆነ የእርሱ ምስክርነት ተቀባይነት የለውም ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ስለ እስራኤል አምላክ ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ ምስክርነቶችን ሰጥቷልና

♦ንጉሱ ስለ እግዚአብሔር ይህንን ትክክለኛ መረዳት ከየት አመጣው?

ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው፥ ንጉሱ ስለ እግዚአብሔር፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መረዳቶች አሉት። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ሊያገኛቸው የሚችለው ከአንድ ምንጭ ብቻ ነው። ከእነ ዳንኤል

እነ ዳንኤል አምላካቸውን እግዚአብሔርን በታማኝነት የሚያገለግሉ ጻድቃን ናቸው። በዚህም ምክንያት ለአሕዛብ ስለ እግዚአብሔር አውሩ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ይከተላሉ። ስለዚህ ስለ አምላካቸው እንደሚነግሩት ጥርጣሬ የለውም

*"ክብሩን <u>**ለአሕዛብ**</u>፥ ተአምራቱንም ለወገኖች <u>**ሁሉ ንገሩ**</u>።" (መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 16:24)*

*"**እግዚአብሔርን** አመስግኑ ስሙንም ጥሩ፥ **ለአሕዛብም ሥራውን አውሩ**።" (መዝሙረ ዳዊት 105:1)*

ይህንንም እውነት በዳንኤል ሕይወት ውስጥ እንመለከተዋለን። ንጉሱ፥ የነ ዳንኤል አምላክ ምስጢርን ገላጭ መሆኑን ሲመሰክር አይተናል። አምላካቸው ምስጢር ገላጭ መሆኑን በምን አወቀ?

*"**ንጉሡም** ዳንኤልን። ይህን ምሥጢር ትገልጥ ዘንድ ተችሎሃልና በእውነት **አምላካችሁ** የአማልክት አምላክ፥ የነገሥታትም ጌታ፥ **ምሥጢርም ገላጭ ነው** ብሎ ተናገረው።" (ትንቢተ ዳንኤል 2:47)*

➢ ንጉሱ አምላካቸው ምስጢር ገላጭ መሆኑን ሊያውቅ የቻለው፥ ዳንኤል ስለነገረው ነው። ይህ በተጨባጭ ስለ እግዚአብሔር ያለውን ትክክለኛ መረዳት በሙሉ ከየት እንደሚያገኝ በግልጽ ያሳያል።

*"27፤ ዳንኤልም **በንጉሡ** ፊት መልሶ እንዲህ **አለ**። ንጉሡ የጠየቀውን ምሥጢር ጠቢባንና አስማተኞች የሕልም ተርጓሚዎችና ቃላተኞች ለንጉሡ ያሳዩ ዘንድ አይችሉም፤ 28፤ **ነገር ግን ምሥጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ**፥ እርሱም በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነፆር አስታውቆታል። በአልጋህ ላይ የሆነው ሕልምና የራስህ ራእይ ይህ ነው።" (ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 2:27-28)*

ንጉሱ እግዚአብሔር ምስጢርን የሚገልጥ አምላክ መሆኑን ሊያውቅ የቻለው ዳንኤል ስለነገረው ነው። እግዚአብሔር ምስጢርን የሚገለጥ አምላክ መሆኑ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝ አስተምህሮ ነው። በዮሴፍ ዘመን የፈርዖንን ሕልም ለዮሴፍ ገልጦለታል። (ዘፍ 41) ስለዚህ እያንዳንዱ እስራኤላዊ እግዚአብሔር ይህን እንደሚያደርግ ያውቃል። ናቡከደነፆርም ይህን ነገር ከዳንኤል ሰምቶ መመስከሩን ስንመለከት፥ ዳንኤልና ወዳጆቹ ስለ አምላካቸው ስለ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ይነግሩትና ያሳውቁት እንደነበር እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

✏ በተጨማሪም ዳንኤል በጸሎቱ እግዚአብሔር በነገስታት ላይ ስልጣን እንዳለው፥ እነርሱን የሚሾምና የሚሽር መሆኑን ሲናገር እንመለከታለን

*"ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል፤ **ነገሥታትን ያፈልሳል፥ ነገሥታትንም ያስነሣል**፤ ጥበብን ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል።" (ትንቢተ ዳንኤል 2:21)*

ይህ ንጉሱ ስለ እግዚአብሔር ያለውን ትክክለኛ እውቀት በሙሉ ከነ ዳንኤል እንዳገኘው የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነው። ምክንያቱም ንጉሱም እንደ ዳንኤል የእስራኤል አምላክ የነገስታት ጌታ መሆኑን በመመስከር፥ እግዚአብሔር በነገስታት ላይ ስልጣን እንዳለው

መስክሯልና። ይህ ስለ እግዚአብሔር ያለውን ትክክለኛ እምነት ከነ ዳንኤል ለማግኘቱ ግልፅ ማስረጃ ነው።

*"**<u>ንጉሡም</u>** ዳንኤልን። ይህን ምሥጢር ትገልጥ ዘንድ ተችሎሃልና በእውነት አምላካችሁ የአማልክት አምላክ፥ **<u>የነገሥታትም ጌታ</u>**፥ ምሥጢርም ገላጭ ነው ብሎ ተናገረው።" (ትንቢተ ዳንኤል 2:47)*

♦ ስለዚህ ንጉሱ ስለ እስራኤል አምላክ ያለውን ትክክለኛ መረዳት በሙሉ ከየት እንደሚያገኘው እርግጠኞች መሆን እንችላለን ማለት ነው። ከነ ዳንኤል ነው። ስለዚህ መልአኩም የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውንም መረዳት ያገኘው ከእነርሱ ነው ማለት ነው።

የእስራኤል አምላክ ልክ እንደርሱ ከመታወቅ በላይ የሆነ ቅዱስ ልጅ እንዳለው (ምሳ 30:4 ኢያ 5:15 ዘጽ 3:2-6) ያም ልጁ መልአኩ እንደሆነ (መሳ 13:18 ዘፍ 32:30) ከእርሱም ጋር በባህርይ አንድ እንደሆነ (ዘጽ 23:21)፥ ህዝቡንም ለማዳን እንደሚልከው (ኢሳ 63:9 2 ዜና 32:21-22 ዘጽ 23:20) ለንጉሱ የማይነግሩበት ምንም ምክንያት የለም። ስለ መልአኩ የተናገራቸው ነገሮች በሙሉ እውነት ናቸውና

► ጥንታዊ የቤተክርስቲያን አበው ዳንኤል 3:25-28 በተመለከተ ምስክርነታቸውን እንደሚከተለው ሰጥተዋል፦

“The heathen king saw in the fire, together with the three Hebrew children, the form of a fourth, like as of an **<u>angel</u>**, (Daniel 3:25) and because he thought that this angel excelled all angels, he judged Him to be the **<u>Son of God</u>**, Whom he had not read of, but in Whom **<u>he believed</u>**"

(Ambrose’s Exposition of the Christian Faith Book 1 Ch. 13)

► የአይሁድ ተንታኞችም በዳንኤል 3:25 ዙሪያ ላይ የሚከተለውን ሀተታ ሰጥተዋል፦

**<u>is like [that of] an angel</u>**:- It is like the **<u>angel</u>** i saw when i was with sannecherib, when his armies were burned, as it is said (2 Kings 19:35): "[And an angel of The Lord went forth] and slew...of the camp of **<u>Assyria</u>**" and Nebuchadnezzar was there and fled among the ten who fled from them.

(Rashi's commentary on Daniel 3:25)

በዚህ ስፍራ እውቁ የአይሁድ ተንታኝ ራሺ (ራባይ ሽሎሞ ይትሳኽ) በዳን 3 ላይ ተገልጦ ንጉሱ የተመለከተው መልአክ፥ በነ ንጉሥ ሕዝቅኤል ዘመን በእግዚአብሔር ተልኮ አሦራውያንን

ያጠፋው መልአክ ነው ይለናል። ይህ ማለት በዚህ ስፍራ ሶስቱን እስራኤላውያንን ያዳነው መልአክ፥ በነ ንጉስ ሕዝቅኤል ዘመን ተገልጦ ይሁዳን ከአሦር ያዳነው መልአክ ነው ማለት ነው። ነገር ግን ያን ግዜ የተገለጠው መልአክ እግዚአብሔር ተብሎ ተጠርቷል (ሆሴ 1:7) ደግሞም እስራኤልን ለማዳን የሚወርደው እግዚአብሔር እርሱ መሆኑ ተነግሯል (ኢሳ 31:4) ይህ ማለት፥ እነ ዳንኤልን ያዳናቸው መልአክ በነ ንጉሥ ሕዝቅኤል ዘመን ይሁዳን ያዳነው አምላክ ነው ማለት ነው። (በዚህ ርዕስ የበለጠ ማስረጃ ለማግኘት እነዚህን ማስፈንጠሪያዎች ይጫኑ፦ ክፍል 1, ክፍል 2)

ስለዚህ በዳንኤል 3 ላይ ለነ ዳንኤል ተገልጦ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ የተገለፀው የእግዚአብሔር መልአክ፥ በመላው ብሉይ ኪዳን የተተረከው የእስራኤል አምላክ ነው ማለት ነው።

► መደምደሚያ

የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ነጻ ያወጣው አምላክ እርሱ ያዳነው ሕዝብ ካወቀው አምላክ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለና እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ መሆኑን በባሪያው በሙሴ አማካኝነት ተናግሯል። ይህ ግልጽ ማስጠንቀቂያ በዘመናት መካከል የማይለወጥ ሲሆን፥ እውነተኛው አምላክ ማን እንደሆነ የምናውቅበት መስፈርት ነው። የመጀመሪያው የእስራኤል ሕዝብ ካወቀው አምላክ የተለየ ወይንም ያንን አምላክ ያልሆነ የትኛውም አካል እውነተኛ አምላክ አይደለም። ብቸኛው ሕልው የሆነው አምላክ (The only God who exists) የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ያዳነው አምላክ ነው። በተጨማሪም ቃሉ እንደሚያስተምረን፥ ከዚህ እስራኤል ካወቀው አምላክ የተለየ ሌላ አምላክን የሚሰብክ ነቢይ ወይንም አላሚን የእስራኤል ሕዝብ እንዳይሰማውና እንዲገድለው እግዚአብሔር አዝዟል። አላሚው ወይንም ነቢዩ ተአምራትና ምልክቶችን ሊያሳይ ይችላል፤ ነገር ግን የሰበከው፥ ሕዝቡ እንዲያመልከው ጥሪ ያቀረበው አምላክ እስራኤል ያላወቀው አምላክ ከሆነ ተቀባይነት የለውም። ቃሉም አይሰማም፥ እርሱም መገደል አለበት። ብቸኛውና እውነተኛውን አምላክ እንዲክዱ ጥሪ አቅርቧልና

ታዲያ! ይህ አይነቱ ክልከላ እያለ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መለኮታዊው ልጅ እንደሆነ እና የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ያዳነው አምላክ መሆኑን አዲስ ኪዳን ይናገራል። በአዲስ ኪዳን የተገለጠው የእግዚአብሔር አብ መለኮታዊ ልጅ በብሉይ ኪዳነ ከሌለ፥ አዲስ ኪዳን የማይታወቅ አምላክን የሰበከ የሀሰት መጽሐፍ ይሆን ነበር። በክርስቶስ ያለንም እምነት የተሳሳተ ይሆን ነበር።

ነገር ግን ይህ መለኮታዊው የእግዚአብሔር ልጅ በብሉይ ኪዳን ተገልጧል። የእግዚአብሔር ልጅ እስራኤል ያወቀው አምላክ ነው። በአባቱ ተልኮ፥ በፊታቸው የሄደ፥ ያዳናቸው፥ ኃጢአታቸውን በተመለከተ ስልጣን ያለው፥ እነ ሙሴ ያዩት የእስራኤል አምላክ ነው። እስራኤል ያወቀው

እውነተኛ አምላክ...የእግዚአብሔር ልጅ! እርሱ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ። ስሙ ለዘላለም የተባረከ ይሁን!

♦ በዚህ ምክንያት ነው በመንፈስ ቅዱስ የተጠነሰሱ የአዲስ ኪዳን ጻሓፊያን እስራኤልን ከግብፅ ያወጣው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የተናገሩት፦

*"ከእነርሱም አንዳንዶቹ **ጌታን** እንደ ተፈታተኑት በእባቦቹም እንደ ጠፉ **ጌታን** አንፈታተን።" (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10:9)*

*"9 Neither let us tempt **Christ**, as some of them also tempted, and were destroyed of serpents." (1Corinthians 10:9)*

በዚህ ስፍራ ሐዋርያው ጳውሎስ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ የተፈታተኑት ጌታ ክርስቶስ መሆኑን በመግለፅ፥ ኢየሱስ እስራኤልን ከግብፅ ያወጣው አምላክ መሆኑን መስክሯል። ያኔ የነበረ፥ እስራኤል የተፈታተኑት፥ በዚያም ምክንያት በኃጢአታቸው የፈረደባቸው አምላክ ክርስቶስ ነው። ይህ ክርስቶስ በሙሴ ዘመን እስራኤልን ሲመራ የነበረ፥ እስራኤልንም ከባርነት ቤት ያወጣው አምላክ መሆኑን ያረጋግጣል።

*"4፤ ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንንና **ጌታችንንም** ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ። 5፤ ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ **ጌታ ከግብፅ አገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ።"** (የይሁዳ መልእክት ምዕራፍ 1:4-5)*

*"4 For there are certain men crept in unawares, who were before of old ordained to this condemnation, ungodly men, turning the grace of our God into lasciviousness, and denying the only Lord God, and **our Lord Jesus Christ.** 5 I will therefore put you in remembrance, though ye once knew this, how that **the Lord, having saved the people out of the land of Egypt, afterward destroyed them that believed not.**" (Jude chapter 1:4-5)*

በዚሁ ስፍራም ሐዋሪያው ይሁዳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን ከግብፅ አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ሲያሳስበን እንመለከታለን። ይህ ማለት የእግዚአብሔር ልጅ እስራኤልን ከግብፅ ያወጣው፥ ከባርነት ቤት ያዳነው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። በሌላ በምንም መልኩ ሊብራራ አይችልም። ጌታ ኢየሱስ ያኔ የነበረ፥ ሕዝቡን ከግብፅ ያወጣው እስራኤል ያወቀው አምላክ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ...እውነተኛው አምላክ! ስሙ ለዘላለም የተባረከ ይሁን!

ስለዚህ አዲስ ኪዳን፥ ከአብ ጋር የነበረ (ዮሐ 1:1-3) ሁሉን የፈጠረ (ቆላ 1:13-15 ዮሐ 1:1-3

ዕብ 1:13 1 ቆሮ 8:6 ዕብ 1:8-10) ከአብ ጋር አንድ ባህርይ የሆነ (ፊሊ 2:6 ዮሐ 10: 28-30 ቆላ 1:15 ዕብ 1:3) አምላክ የሆነ (ዕብ 1:8 ዮሐ 1:1) መለኮታዊ **ልጅ** እንዳለ ማስተማሩ ትክክል ነው። የእስራኤልን አምላክ እየተረከ ነው። ትክክለኛው እስራኤል ያወቀው አምላክ እርሱ ነውና። እኛ ክርስቲያኖች  የአብርሃምን አምላክ አልተውንም፥ ወይንም በሌላ አልቀየርነውም። የአብርሃም አምላክ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ የኛም አምላክና ጌታ ነው!

ይህ ጌትነቱ በብሉይም በአዲስም ኪዳን የተመሰከረለትን አምላክ ያልተቀበላችሁ ሁሉ ዛሬ እንደ ጌታችሁና እንደ አዳኛችሁ ትቀበሉት ዘንድ የዘወትር ጸሎታችን ነው!

*"ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ **ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ** እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም **በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ** ዘንድ ይህ ተጽፎአል።" (የዮሐንስ ወንጌል 20:31)*

*"**ልጁ** ያለው **ሕይወት አለው**፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።" (1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5:12)*

**ጌታ ኢየሱስ ያድናል!**

# ተፈጸመ